# አዲስ ዘመን

እንድ

ማክሰኞ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 228 ሚያዝያ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# «ሃገራዊ ምክክሩን ለማሳካት የተረጋጋ ሰላምና አስተማማኝ ደህንነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል»

- አቶ አባተ ኪሾ



ፎቶ - እዮብ ተፈራ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሃገራዊ ምክክሩን ለማሳካት የተረጋጋ ሰላምና አስተማማኝ ደህንነት ማረጋገጥ እንደሚገባ የቀድሞ የደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አባተ ኪሾ አመለከቱ። በሃገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ በተገቢው መወጣት አለበትም ብለዋል።

አቶ አባተ ኪሾ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ ሃገራዊ ምክክር ለማካሄድ የታሰበው በሃገሪቱ መቀረፍ ያለበት አሳሳቢ ችግር በመኖሩ ነው። በየጊዜው እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች መንስዔም አለመግባባቶች በመኖራቸው ነው። መንግሥትም በጉዳዩ ዙሪያ ተደጋጋሚ መግለጫ አውጥቷል፤ በአንዳንድ አካባቢዎችም እርምጃ እየወሰደ ይገኛል ብለዋል።

ከሁሉም በላይ ግን አለመግባባቶቹን ለመፍታት አይነተኛ መፍትሄ የሆነውን ሃገራዊ ምክክር ለማካሄድ የተረጋጋ ሰላምና አስተማማኝ ደህንነት መፍጠር የሁሉም ኃላፊነት መሆን እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

መንግሥት የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ቀዳሚ ተግባሩ በመሆኑ ሰሞኑን የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት በጉዳዩ ዙሪያ ያወጣው መግለጫ የዚሁ አካል መሆኑን የጠቀሱት አቶ አባተ፤ በአሁኑ ጊዜ የዜጎች ደህንነትና ሃገራዊ አንድነቱን እየፈተነ ያለው ችግር ከስር መሠረቱ ለመፍታት ሃገራዊ ምክክር ማካሄድ መፍትሔ ነው። ለዚህ ደግሞ መንግሥት በልዩ ትኩረት መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል።

«ሃገራዊ ምክክሩን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









# ለትግራይ የሚላከው እርዳታ ለሕዝቡ ሳይሆን ለሕወሓት ታጣቂዎች እየዋለ መሆኑን ትዴፓ ገለጸ

- የትግራይ ሕዝብ ሰቆቃ የሚያበቃው ሕወሓታዊ አስተሳሰብ ሲጠፋ ብቻ ነው



ፎቶ - ሐዲስ አብርሃ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ለትግራይ ሕዝብ የሚላከው እርዳታ ለሕዝቡ ሳይሆን ሕወሓት ራሱ ላደራጃቸው መደቦችና ታጣቂዎች እየዋለ መሆኑን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ገለጸ። የትግራይ ሕዝብ ሰቆቃ የሚያበቃው ሕወሓታዊ አስተሳሰብ ሲጠፋ ብቻ እንደሆነም ተመላክቷል።

የትግራይ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰብዓዊ እርዳታ ወደ ትግራይ ክልል የሚላክ ቢሆንም ለሕዝቡ የሚደርስ እርዳታ የለም። እርዳታው ወደ ትግራይ ክልል ቢገባም ለሕዝቡ እየደረሰ አለመሆኑን ይልቁንም ለሕወሓት ታጣቂዎች እየተሰጠ መሆኑን ፓርቲያቸው ከተለያዩ ምንጮች እንዳረጋገጠ ገልጸዋል።

በሕዝብ ስም መነገድ የሕወሓት የዛሬ ባህሪው ብቻ ሳይሆን ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ታሪክ እንደሚያስረዳ የገለጹት አቶ ሙሉብርሃን፤ ወደ ትግራይ ክልል የሚገባው የምግብ፣ መድኃኒትና ሌሎች መሰል እርዳታዎች እየዋሉ ያሉት ለትግራይ ሕዝብ

ለትግራይ የሚላከው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







የውስጥና የድንበር ዘለል የጸጥታ ችግሮችን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሲሠሩ እንደሚገባ ክልሉ አሳሰበ — ገፅ 2

«የሩስያና የዩክሬን ግጭት እንደ ሃገር ራስን በምርት ለመቻል ለሚደረገው ጥረት እድል አምጥቷል» - አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ — ገፅ 3

ከኢድ እስከ ኢድ መርሐ ግብር ዲያስፖራው ከሃገሩ ጎን መቆሙን የሚያሳይበት ዕድል ነው - ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ — ገፅ 4








# የውስጥና የድንበር ዘለል የጸጥታ ችግሮችን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሊሠሩ እንደሚገባ ክልሉ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ የሚከሰቱ የውስጥና የድንበር ዘለል የጸጥታ ችግሮችን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ሊሠሩ እንደሚገባ የጋምቤላ ክልል አሳሰበ።

የጋምቤላ ክልል መንግሥት የፀጥታ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን ትናንትና በጋምቤላ ከተማ አካሂዷል።

በወቅቱ የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ ፤ በክልሉ የውስጥና የድንበር ዘለል የጸጥታ ችግሮችን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች ከደቡብ ሱዳን ጋር በሚዋሰነው የጋምቤላ ክልል ውስጥ በመግባት በነዋሪዎች ላይ ከሚፈጸሙት ጥቃት በተጨማሪ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የቀንድ ከብቶች በተደጋጋሚ ዘርፈው ሲወስዱ እንደነበር አስታውሰዋል።

የጥፋት ኃይሎች በክልሉ አንዳንድ አካባቢዎች ሊያደርሱ የሚችሉትን ጥፋት ለመከላከል መንግሥት በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ራሱን የጋምቤላ ነፃነት ግንባር /ጋነግ/ ብሎ የሚጠራው የአሸባሪዎቹ ሕወሓትና ሸኔ ተላላኪ እኩይ ሴራውን ለማምከን የተለያዩ የጸጥታና ደህንነት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተያያዘ የሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን ጨምሮ በክልሉ ጠረፋማ አካባቢዎች የደቡብ ሱዳን የሙርሌ ጎሳ አባላት የሚፈጽመውን ወንጀሎች በመከላከል ረገድ ከጸጥታ አካላቱ ከፍተኛ ኃላፊነት እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

በክልሉ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈንና ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ለመግታት ለሚደረገው ጥረት ስኬታማነት ማኅበረሰቡ ሁለንተናዊ ተሳትፎውን



**አቶ ኡሞድ ኡጁሉ**

እንዲያጠናክር አቶ ኡሞድ ጥሪ አቅርበዋል።

በመድረኩ የክልሉና የአካባቢው የፀጥታ ሁኔታ የተገመገመ ሲሆን፤ ከውስጥ የፀጥታ ሁኔታ የከተማው የሌብነት፣ ስርቆትና ተራ ወንጀሎች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

በተጨማሪም ሸኔ እና ራሱን የጋምቤላ ነፃነት ግንባር (ጋነግ) ብሎ የሚጠራው ድርጅት እንቅስቃሴን በተመለከተ ውይይት ተካሂዷል።

የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች ጥቃትና እንቅስቃሴ በድንበር አካባቢ የደቡብ ሱዳን አማፅያን ኃይሎች እያደረሱ ያለውን ጥቃት በተመለከተ ውይይት በማካሄድ አቅጣጫ መቀመጡን ክልሉ አስታውቋል።

# «ፍቼ ጨምበላላ የቱሪስት መስህብ ከመሆኑ ባሻገር የፍቅርና የይቅርታ በዓል ነው»

*- መምህርና ደራሲ አለሙ ኪርባ*

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ የፍቼ ጨምበላላ በዓል የቱሪስት መስህብ ከመሆኑ ባለፈ የፍቅርና የይቅርታ በዓል ነው ሲሉ መምህርና ደራሲው አለሙ ኪርባ ገለጹ።

መምህሩ የዘመን መለወጫ በዓሉን ትውፊትና ዕሴቱን በጠበቀ መንገድ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባም አሳስበዋል።

መምህርና ደራሲ አለሙ ኪርባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ፍቼ ጨምበላላ ብዙዎች ሊታደሙበት የሚመኙት የፍቅር፣ የሰላም፣ የመረዳዳትና የይቅርታ በዓል ነው።

በዓሉ የአንድነትና የመተሳሰብ በመሆኑ ፍቼ ጨምበላላን የሚያከብር ሁሉ የበዓሉን ዕሴት በጠበቀ መልኩ ችግረኞችን በመርዳትና በመደጋገፍ ሊሆን እንደሚገባውም መምህር አለሙ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ፍቼ ጨምበላላ ስለ ሃገር ሰላም፣ ስለ አዝመራው ደህንነት እንዲሁም ስለእንስሳቱ ጤንነት እንዲሁም ስለ መላው ሃገር ወደ ፈጣሪ የሚለመንበት ክብረ በዓል ነው ብለዋል።

በዓሉ ኢትዮጵያውያን ሰላማቸውን፣ ፍቅር አንድነትና ወዳጅነታቸውን የሚያጠናክሩበት ነው ያሉት መምህሩ፤ በመሆኑም በዓሉን ስናከብር በመዋደድና ሰላምን በመፈለግ መንፈስ መሆን አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

የፍቼ ጨምበላላ በዓል የሲዳማ ብሔር የማንነቱ መገለጫ ነው። ይሁንና በተለያዩ ጊዜያት የብሔሩ መገለጫ የሆነው ፍቼ ጨምበላላ እንዳይከበር በርካታ ፈተናዎች ይጋረጡ ነበር። እነዚያን ተግዳሮቶች ታልፈው አሁን ላይ በነጻነት እንዲከበር መደረጉ አስደሳች ነው ብለዋል።

አባት ቅድመ አያቶች እስከዛሬ ያደረሱትን የፍቼ ጨምበላላ በዓል ትውፊት በሥነሥርዓት ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።



የፍቼ ጨምበላላ በዓል በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት /ዩኔስኮ/ ከማይዳሰሱ የሰው ልጅ ወካይ ቅርሶች መካከል አንዱ ሆኖ ተመዝግቧል።

የሲዳማ ሕዝብ የጨረቃና ከዋክብትን አቀማመጥ በማጥናት አዲስ ዓመት ያከብራል። በዓሉም ፍቼ ጨምበላላ ይባላል። በዓሉ በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት ሲከበር የቆየ ሲሆን ባለፉት ሁለት ዓመታት በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት በአደባባይ ሳይከበር ማለፉ ይታወሳል።

የ2014 ፍቼ ጫምበላላ በዓል በዓሉ እሴቱን በተጠበቀ መልኩ ሚያዚያ 20 እና 21 ቀን 2014 ዓ.ም እንደሚከበር በ"ጉዱማሌ" ወይም በባህላዊ አደባባይ፣ በቄጣላና በተለያዩ ውብ ባህላዊ ክንዋኔዎች እንደሚከበር የሲዳማ ክልል አስታውቋል።

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ለመላው የሲዳማ ሕዝብ እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዓሉን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።







**ለሶማሌና ለኦሮሚያ ክልል ድጋፍ ተደርጓል**

# ሚኒስቴሩ በሶማሌና ኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ድጋፍ አደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር በሶማሌና ኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ድጋፍ አደረገ።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር በሶማሌ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሚውል ከአምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል።

ድጋፉ በሶማሌ ክልል በተከሰተው ድርቅ አስከፊ ጉዳት ለደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደሚውል ሚኒስቴሩ አሳውቋል።

ድጋፉን የተረከቡት የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሐመድ ፤በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ዝናብ እየጣለ በመሆኑ ለአርብቶ አደሩ የሚሆን እርጥበት እየተገኘ መሆኑን ጠቁመው፤ ይሁንና በተከሰተው ድርቅ የተነሳ አሁንም ከፍተኛ ድጋፍ የሚሹ ዜጎች አሉ ብለዋል።

ሚኒስቴሩ ያበረከተውን ድጋፍም ለድርቁ ምላሽ ለመስጠት እንጠቀምበታለን ሲሉ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድና የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ብርሃኑ ሌንጂሶ በጅግጅጋ ከተማ በመገኘት ለ400 ሰዎች የኢፍጣር መርሐ ግብር አካሂደዋል።

በኢፍጣር መርሐ ግብሩ ላይ የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሌሎች የክልሉ መንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገኝተዋል።

በተመሳሳይ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስትር በኦሮሚያ ክልል በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች የሚውል ስድስት ሚሊዮን 394 ሺህ ብር የሚጠጋ ገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ ድጋፉን ባስረከቡበት ወቅት፤ በቆላማ አካባቢ የሚኖረው ማኅበረሰብ እንዲያገግም የተጀመረው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

ሚኒስቴሩ በኦሮሚያ ክልል በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ድጋፉን የተረከቡት የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው፤ ለተደረገው ድጋፍ አመስግነው መንግሥት በድርቅ የተጎዱ ወገኖችን በዘላቂነት ለማቋቋም እንደሚሠራ ገልጸዋል።

# «የሩስያና የዩክሬን ግጭት እንደ ሃገር ራስን በምርት ለመቻል ለሚደረገው ጥረት እድል አምጥቷል»

## - አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- የሩስያና የዩክሬን ግጭት ኢትዮጵያን በኢኮኖሚ ቢጎዳትም እራስን ለመቻል አስገድዶም ቢሆን እድል አምጥቷል ሲሉ የፌርፋክስ አፍሪካ ፈንድ ድርጅት ሊቀመንበር አቶ ዘመዴነህ ንጋቱ ገለጹ።

አቶ ዘመዴነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የሩሲያ እና የዩክሬን ግጭት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ተፅዕኖ ቢያሳርፍም አስገድዶም ቢሆን ራስን በምርት ለመቻል እድሉን አምጥቷል። እራስን መቻል ላይ ባሉን አማራጮች ሁሉ አጥብቀን እንድንሠራ ያደርጋል ብለዋል።

የአገራቱ ግጭት ከጀመረ በኋላ ኢትዮጵያን ጨምሮ በዓለም ላይ የሸቀጦች ዋጋ ጨምሯል ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ ስንዴንና መሰል ግብዓቶችን ከነሱ ያስገቡ የነበሩ ሃገራትና ኢትዮጵያ ራስን ለመቻል የሚያደርጉትን በሃገር ውስጥ የማምረት ትጋት ሸፋን እንዲሳድጉ ያደርጋል። ግጭቱም በክፉ ቀን የተገኘ መልካም አጋጣሚን ይዞ መጥቷል ብለዋል።

ግጭቱ የኢትዮጵያን የምግብ፣ ኢነርጂና ሌሎችም ቁሳቁሶች የዋጋ ግሽበት ከፍ አድርጎታል። ከውጭ የሚገቡ እቃዎች ቀድሞውኑ ሲገቡም ጭምር ዋጋቸው ስለሚጨምርና የነዳጅ ዋጋም እየጨመረ በመምጣቱ የግሽበት ምጣኔ በፍጥነት እንደሚጨምር ገልጸዋል።

ከውጭ የሚገቡ እቃዎች የዋጋ ግሽበትን በማባባስ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራሉ ያሉት አቶ ዘመዴነህ፤ በተለይም የምግብ ነክ ግብዓቶች ግሽበትና የምግብ ዋጋ ይጨምራል፤የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይም ተፅዕኖ ያሳድራል ብለዋል።

በዚህ ወቅት ኢትዮጵያና ሌሎች ታዳጊ ሃገራት የአቅርቦት እጥረት ገጥሟቸዋል። የዋጋ ግሽበት በኢኮኖሚያቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል። በኤክስፖርት በኩልም የዓለም የኢኮኖሚ እድገት ፍጥነትን ይቀንሳል፣ ግጭቱ ለግሽበቱ ብቸኛው ምክንያት እንደማይሆንም አቶ ዘመዴነህ ገልጸዋል።

በእነሱ ግጭት ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ስንዴ ከውጭ ማስገባትን ለማቆም እንድታቅድ አድርጓታል። ይህም ለኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ ነው። በግጭቱ ከነሱ የሚቀርቡ አቅርቦቶች መቋረጥና ግሽበት መከሰቱ የኢትዮጵያን እቅድ ሊያፋጥን ይችላል።

ኢትዮጵያም ከሰሃራ በታች ካሉት የአፍሪካ ስንዴ አምራቾች ቀዳሚ ሃገር ነች። አሁን የተፈጠረው የዓለም ሁኔታም አስቀድሞ በዕቅድ የተያዘውን  በአጭር ጊዜ ለማሳካት አጠናክረን እንድንሠራ እድሉን አግኝተናል ብለዋል።

የግጭቱ ሁኔታዎች ተገደዶ ራስን የመቻል ስልትን እንድናስብ ያደረገ ነው። ስልቱም በጭንቅ ቀን የሚነደፍ ነው። እንደ ሃገር ቀደም ሲል የታሰበውን ራስን የመቻል ስትራቴጂን በማፋጠንና የሃገር ውስጥ ምርትን በማሳደግ ሁሉንም ነገር ከውጭ የማስገባት ሂደት የነበረውን ተጽዕኖ በሃገር ውስጥ ለመተካት ያስችላል።

ወቅታዊ የዓለም ሁኔታ ሃገራት በኢነርጂ ዘርፍም የነበራቸውን አተያይ ይቀይራል የሚሉት አቶ ዘመዴነህ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢነርጂ የሚመረተው ምንም አይነት ዘይት ሳይጠቀም ከታዳሽ ኃይል ነው። ስለሆነም አሁን ኢትዮጵያ ከነዳጅ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎች ወደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ለመሸጋገር ትልቅ ስትራቴጂን ተግባራዊ እንድታደርግ ሊያስችል ይችላል። ከዘይት የበለጠ የኤሌክትሪክ ኃይል አጠቃቀም በጣም አስፈሪ ስትራቴጂ ነው። በኢትዮጵያም አሁን በተፈጠረው ችግር ሳቢያ መተግበር ሊጀምር ይገባዋል ብለዋል።

በዚህ ወቅት የገጠሙንን የኢኮኖሚ ችግሮች ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፣ ከዓለም ባንክ እና ከሌሎች ድጋፍ አድራጊዎች የሚገኘውን ድጋፍ በተገቢው መንገድ በመጠቀም፣ ችግር የወለዳቸው ሃገር በቀል መፍትሔዎችን ለዘላቂ እድገትና መፍትሔ እንዲውሉ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

# በቀጣዮቹ 10 ዓመታት 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ ይሠራል

- **በአሁኑ ወቅት 2 ሚሊዮን የመኖሪያ ቤቶች እጥረት አለ**

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በራሱ ከሚገነባቸው ቤቶች በተጨማሪ ሌሎች አጋር አካላትን በማሳተፍና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በቀጣዮቹ 10 ዓመታት 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ቤቶች  እንዲገነቡ እንደሚሠራ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ገለጸ።

ለኑሮ ምቹ ያልሆኑና ፈርሰው መሠራት ያለባቸውን አንድ ሚሊዮን ቤቶችን ሳይጨምር በአሁኑ ወቅት የሁለት ሚሊዮን ቤቶች እጥረት እንዳለም ተገልጿል።

በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ አቶ ታደሰ ከበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት በራሱ ከሚገነባቸው በተጨማሪ ሌሎች አጋር አካላትን በማሳተፍና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በቀጣዮቹ 10 ዓመታት 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ቤቶችን እንዲገነቡ ይሠራል።

አሁን ባለው ደረጃ በከተሞች ያለው የቤት አቅርቦት እና ፍላጎት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ ለዚህም ከተሞች በፈጣን ዕድገት ውስጥ መገኘታቸው እና የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱን እንደምክንያት አንስተው የቤት አቅርቦቱን በሚፈለገው ልክ ማስኬድ እንዳልተቻለ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ታደሰ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ የቤት እጥረት ከመኖሩም በተጨማሪ በከተሞች ያሉ አንድ ሚሊዮን ለመኖር ምቹ ያልሆኑ ቤቶች አሉ። በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥም ወደ ሶስት ሚሊዮን አካባቢ ቤቶች ተጨማሪ ፍላጎት እንደሚኖር መገመቱን ተከትሎ በአጠቃላይ ስድስት ሚሊዮን አካባቢ ቤቶች በ10 ዓመት ውስጥ መገንባት ያስፈልጋል። ሆኖም የሃገሪቱ አቅም ስድስት ሚሊዮን ቤቶችን ለመገንባት የማይፈቅድ በመሆኑ በመንግሥት ዕቅድ መሠረት በቀጣዮቹ 10 ዓመታት 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ቤቶች እንዲገነቡ ይሠራል ብለዋል።

የቤቶች ግንባታ የሚከናወነው በመንግሥት ብቻ ሳይሆን ሌሎች አጋር አካላትን ጭምር በማሳተፍ ነው ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ መንግሥት፣ ግለሰቦች፣ የቤት ማኅበራት፣ ሪል ስቴት አልሚዎች እና ሌሎችንም በማሳተፍ እና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመቅረፍ እንደሚሠራ ተናግረዋል። በተጨማሪም በመኖሪያ ቤት ዘርፍ ላይ መንግሥትና የግል ባለሀብቶች በጋራ የሚያለሙበት መንገድ የሚመቻች መሆኑን አመላክተዋል።

ለዚህ የመጀመሪያው እርምጃ የቤቶች ልማት ስትራቴጂን ማስተካከል አስፈላጊ እንደነበር የገለፁት አቶ ታደሰ፤ ስትራቴጂው ሁሉም አካላት እንዲሳተፉ የሚያስችል ሆኖ መቀረጹንና ለአስፈጻሚው አካል መቅረቡን ተናግረው እንደሚያጸድቅ እየተጠበቀ መሆኑን አስረድተዋል።



አቶ ታደሰ ከበበ

እንደ አቶ ታደሰ ገለፃ፤ 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ቤት ግንባታን በተለመደው አሠራር ማሳካት ስለማይቻል አሁን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጀመሩ የተገጣጣሚ ቤት ቴክኖሎጂዎች በክልል ከተሞችም ተስፋፍተው እንዲሠሩ ለማድረግ ክልሎች ከከተማ አስተዳደሩ ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

የተገጣጣሚ ቤቶች ቴክኖሎጂ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሚፈለገው ጥራት፣ ብዛትና በጀት ማጠናቀቅ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ ሌሎች ቴክኖሎጂዎችንም ወደ ዘርፉ በማስገባት የቤት ችግሩን ለመቅረፍ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

ምንም እንኳን የመኖሪያ ቤት እጥረት በሃገሪቱ በሁሉም ከተሞች ላይ ያለ ቢሆንም እጥረቱ በተለይ በአዲስ አበባ እና ኢንዱስትሪዎች ተስፋፍተው በሚገኙባቸው እንደ ሀዋሳ፣ አዳማ፣ ባሕር ዳርና የመሳሰሉ ከተሞች ይብሳል ተብሏል።

መንግሥት፣ ዜጎች ቤት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት ያሉት አቶ ታደሰ፤ 4 ነጥብ 4 ሚሊዮን ቤቶችን በ10 ዓመታት ውስጥ ለመገንባት ዕቅዱን ማፅደቁ ዜጎች የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል ብለዋል።



አቶ አወል ሱልጣን

# የፍትሕ አካላት የሐሰተኛና ጥላቻ ንግግር ወንጀልን የሚፈጽሙ ሰዎችን ለሕግ እንዲያቀርቡ ተጠየቀ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የፍትሕ ሚኒስቴርን ጨምሮ ፖሊስ፣ የክልልና የፌዴራል የፍትሕ ተቋማት የሐሰተኛና ጥላቻ ንግግር ወንጀልን የሚፈጽሙ ሰዎችን ወደ ሕግ ማቅረብ እንዳለባቸው ተጠቆመ።

በፍትሕ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አወል ሱልጣን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ቁጥጥር ተፈጻሚ መሆን በሚገባው ደረጃ እየተፈጸመ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል። ከዚህ በኋላ ሐሰተኛ የመረጃ ስርጭትን የሚያሰራጩ ሰዎች በአዋጁ ላይ የተቀመጡትን የወንጀል ቅድመ ሁኔታዎች እስኪያሟሉ ድረስ ፖሊስ ምርመራ መጀመር እንዳለበት፤ ማኅበረሰቡም መጠቆም እንደሚችል፤ ዓቃቤ ሕግም ወንጀል የመመርመርና የመምራት ኃላፊነት ስላለበት በዚህ ሂደት ውስጥም ፖሊስ የወንጀል ምርመራ እንዲጀምርና የተጣራ ምርመራ ካለ ክስ መስርቶ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወስዶ ክርክር ማድረግ እንዳለበት  ገልጸዋል። ይህ በተጨባጭ እንደሚከናወንም ነው ያስታወቁት።

ይህን ማድረግ ባለመቻላችን በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሰዎች ከመስመር ሲወጡና እንዲህ አይነት መረጃዎችን ሲያሰራጩ  ቆይተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በሐሰተኛ መረጃና ጥላቻ ንግግር ዙሪያ ማኅበረሰቡን የማስተማርና የማሳወቅ፣ የሕጉን ይዘት የመግለጽ በርካታ ሥራዎች ሲከናወኑ እንደነበርም  ጠቅሰዋል። በአሁኑ ወቅት አብዛኛው ሃገር ውስጥ የሌሉ ሚዲያዎች በውጭ ሃገር ሆነው፤ ሃገር ውስጥ ያሉት ደግሞ ሐሰተኛ “አካውንት”  እየከፈቱ ብሔርን ከብሔር፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ሊያጋጩ የሚችሉ መልዕክቶች እያስተላለፉ መሆናቸውንና በተገለፀው ልክ እርምጃ እየተወሰደ እንዳልሆነም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አወል ገለጻ፤ አዋጁ ሲወጣ ዋና ዓላማው በሕዝቦች፣ በብሔሮችና ሃይማኖት መካከል ሰዎች ተቻችለው እንዲኖሩና አንደኛው ሌላኛውን በማንነቱ እንዳያጠቃው ለመከላከል ነው። እንዲህ አይነት ድርጊት የሚፈጽሙ አካላት ላይ እርምጃ ለመውሰድ የወጣ አዋጅ ቢሆንም፤ በተጨባጭነት በፌስ ቡክም ሆነ በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች በርካታ የሕግ ጥሰት እየተፈጸመ ነው።

ከዚህ በኋላ ፍትሕ ሚኒስቴር፣ ፖሊስ፣ የክልልም ሆነ የፌዴራል ፍትሕ ተቋማት እንዲህ አይነት ወንጀል የሚፈጽሙ ሰዎችን ለሕግ የማቅረብ ሥራ እንደሚሠሩና በሂደት እየተደራጁ ምርመራው ተጠናክሮ ክስ ተመሥርቶ ወደ ፍትሕ አደባባይ የሚመጡ እንደሚኖሩ ገልጸዋል።

የፍትሕ ሚኒስቴር ሕጉ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ሰፊ ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ያነሱት አቶ አወል፤ ነገሮችን በሆደ ባሻነት አሊያም ነገሮችን እያሳለፉ በመሄድ ማኅበረሰቡ እስኪያውቅና እስኪረዳ፣ እንዲሁም ወንጀለኞችን አሳልፎ መስጠት የሚችለበት ሁኔታ ላይ እስኪደርስ ድረስ የተግባቦት ሥራ መሥራት ላይ ትኩረት አድርገን እየተንቀሳቀስን ነው ብለዋል። በዚህም አብዛኛው ሰው በተለይም ወደ ሚዲያው ቀረብ ያሉት ሰዎች የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የሚያስችል አዋጅ መውጣቱን  ያውቃል ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ አወል እንዳሉት፤ በጉዳዩ ዙሪያ የተወሰነ ለውጥና መሻሻል አለ። በተለይ በቅርብ ጊዜ ሐሰተኛ አካውንት የሚባሉት ካልሆኑ በቀር እውነተኛ አካውንት ያላቸው ሰዎች በተቻለ መጠን የሚያስተላልፏቸው መረጃዎች ላይ በተወሰነ መልኩ መጠንቀቅ መጀመራቸው ግንዛቤ ከመስጠት አኳያ ሕጉ ላይ በስፋት መሠራቱን የሚያሳይ ነው። አሁን ደግሞ ይህንን ተላልፈው ወንጀል የሚሠሩ ሰዎች ከእውቀት ማነስ የሚመነጭ ሳይሆን ሆነ ብለው ወንጀል ለመፈጸም፤ ባልተገባ መንገድ ማኅበረሰብ ውስጥ ረብሻና ግርግር እንዲነሳ ለማድረግ አስበውበት እንደሆነ ተናግረዋል።

# ከኢድ እስከ ኢድ መርሐ ግብር ዲያስፖራው ከሃገሩ ጎን መቆሙን የሚያሳይበት ዕድል ነው

- ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ

**ዳግማዊት ግርማ**



አዲስ አበባ፡- ከኢድ እስከ ኢድ ሃገራዊ ጥሪ መርሐ ግብር ዲያስፖራው በደስታም ሆነ በኃዘን ወቅት ከሃገሩ ጎን መቆሙን የሚያሳይበትን ዕድል ፈጥሯል ሲሉ የመርሐግብሩ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ገለጹ።

ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የከኢድ እስከ ኢድ ሃገራዊ ጥሪ መርሐግብር ዲያስፖራ ማኅበረሰብ ወደሃገሩ ገብቶ ከሕዝቡ ጎን መቆሙን የሚያሳይበት ዕድል መፍጠር ይችላል።

ሃገራዊ ጥሪውን ተከትሎ በመርሐ ግብሩ ለመታደም በርካታ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወደኢትዮጵያ እየመጡ መሆኑን የጠቆሙት ኡስታዝ አቡበከር፤ ዲያስፖራዎቹም ወደትውልድ ሃገራቸው ሲመጡም በደስታና በጥሩ መንፈስ መሆኑን ገልጸዋል።

ሃገራዊ ጥሪውን መሠረት አድርገው የተሰናዱት መርሐግብሮችም ዲያስፖራውን ማኅበረሰብ ያማከሉ ናቸው፤ በመጪው ዓርብ ታላቅ የጎዳና ላይ ኢፍጣር በአዲስ አበባ ይካሄዳልም ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ በመጪው ረቡዕ የኢድ ኤክስፖ በይፋ እንደሚከፈትም ጠቁመው፤ ጥሪውን ተከትሎ ለሚመጡ እንግዶች የሃገሪቷን ተጨባጭ ሁኔታ በተሻለ መንገድ እንዲረዱ የሚያስችል ጉብኝት እንደተዘጋጀላቸውን ገልጸዋል።

በተለይ በጦርነቱ ምክንያት የተጎዱ ዜጎችንና መልሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት እንዲሳተፉና በግጭቶቹ የተነሳ ጉዳት የደረሰባቸውን ቅርሶች ለመጠገን ድጋፍ እንዲያደርጉ ዕድል መመቻቸቱንም ኡስታዝ አቡበከር አህመድ አስታውቀዋል።

በዚህም ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ የትም ቢሄዱ ሃገራቸውን በክፉም ሆነ በደግ ጊዜ ብቻዋን እንደማይተዋት የሚያሳዩበት መልካም ዕድል ተፈጥሯል ሲሉ ተናግረዋል።

በመርሐ ግብሩ የኢትዮጵያን በጎ ጎን ለዓለም ለማስተዋወቅ ጥረት እንደሚደረግ የጠቆሙት ኡስታዝ አቡበከር፤ በተለይ ከእስልምና ጋር ተያይዞ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ በሰፊው እንደሚተዋወቅ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የእስልምና ዕምነት ባለውለታ መሆኗን ይታወቃል። ስለእምነቱ ሲነሳ ከኢትዮጵያ ውጪ መነሳት አለበት ብዬ አላስብም። ኢትዮጵያም የዕምነት ልዩነትን መሠረት ሳታደርግ የነብዩ መሐመድን ባልደረቦች የተቀበለችና በዕምነታቸው የተነሳ መከራ ሲደርስባቸው ጥገኝነት የሰጠች ነፃ ሃገር መሆኗ በታሪክ ይታወቃል ብለዋል።

ይህንንና ሌሎች ታሪኮችን መሠረት ያደረጉ የገጽታ ግንባታ ሥራዎችም በሰፊው እንደሚከናወኑ አስረድተዋል።

መረጃዎቹም ዲያስፖራዎች ወደተለያዩ ሃገራት በሚጓዙበት ወቅት ስለሃገራቸው በቂ ግንዛቤ ይዘው እንዲያስተዋውቁ ያግዛል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በየሄዱበት አቅጣጫ ሁሉ ሃገራቸውን አስቀድመው የሚጓዙ መሆናቸውን ያነሱት ኡስታዝ አቡበከር፤ የኢትዮጵያን ዕውነት ለዓለም የሚያስረዱ አምባሳደሮች በመሆናቸው ክብር ይገባቸዋል ሲሉም ገልጸዋል።

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ገለጻ፤ ከኢድ እስከ ኢድ ሃገራዊ ጥሪን ተከትሎ በሚሰናዱ መርሐግብሮችን ላይ በአስተናባሪነት ለመሳተፍ በርካታ ወጣቶች በበጎ ፈቃደኝነት ተመዝግበዋል። እስካሁን ድረስ በአዲስ አበባ ብቻ የበጎ ፈቃድ መርሐ ግብሩን ዓላማ በአግባቡ እንዲረዱ የተደረጉ ከ2 ሺህ 500 በላይ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች ስልጠና ወስደዋል።

# ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 249 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገቢ ተሰበሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ 267,558,565,762.32 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 248,618,035,417.89 ብር መሰብሰብ መቻሉን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ። ይህም የእቅዱን 93 በመቶ መሆኑ ተነገረ።

ገቢው የተሰበሰበው ከሃገር ውስጥ ታክስ ብር 145,268,523,038.54 ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ብር 103,349,512,379.35 ሲሆን የተሰበሰበው ገቢ ከ2013 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አንጻር ሲታይ የብር 36,310,719,438.79 ወይም 17.10 ከመቶ እድገት ማስመዝገቡ ተጠቁሟል።

የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው የገቢ አፈጻጸሙን አስመልክተው እንዳሉት ይህ የገቢ አፈጻጸም የተመዘገበው ዓለም አቀፉ የኮሮና ወረርሽኝና መሰል ተግዳሮቶች እንዳሉ ሆነው እንደ ሃገር በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆነን የተሰበሰበ ገቢ ነው።

እንደ ተቋም አራት የፌደራል ገቢ ሰብሳቢ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በጦርነቱ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ከሥራ ውጭ በሆኑበትና የተለመደው የንግድ ሥርዓት እንቅስቃሴ በተቀዛቀዘበት ወቅት የተሰበሰበ ገቢ በመሆኑ አፈጻጸሙ እጅግ በጣም የሚያበረታታ እንደሆነ እናምናለን በማለት ተናግረዋል። ይህ ከፍተኛ ውጤት መመዝገብ የተቻለው የገቢዎች ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችና ሠራተኞች ጠዋትና ማታ እንዲሁም ቅዳሜና እሁድ በቁርጠኝነት፣ በኃላፊነት ስሜትና በትጋት፣ መለኪያቸውን ሃገርና ሕዝብ አድርገው በመሥራታቸው በመሆኑ በራሴና በገቢዎች ሚኒስቴር ሥም ምስጋና አቀርባለሁ ብለዋል።

በገቢ አሰባሰቡ ሥራ ውስጥ የተቋማቱ አመራሮችና ሠራተኞች ባሻገር ገቢያቸውን በወቅቱ በማሳወቅ ግብር ለከፈሉ የፌዴራል ግብር ከፋዮች እንዲሁም አጋር አካላትና መላው ሕዝብም ምስጋና አቅርበዋል።

በቀጣይም ለሃገራችሁና ለሕዝባችሁ የምታደርጉት የተለመደው ትብብራችሁ እንዳይለየን ሲሉ ጠይቀዋል።

# ስትግራይ የሚሳከው...

ከገፅ 1 የዞረ

ሳይሆን ሕወሓት ላደራጃቸው መደቦችና ታጣቂዎቹ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ሙሉብርሃን ገለጻ፤ የትግራይ ሕዝብ በረሃብና በበሽታ እያለቀ ነው። በቅርቡ ወደ አማራ ክልል ቆቦና አላማጣ በርካታ ቁጥር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች የገቡ ሲሆን ከተፈናቃዮች አንደበት፣ በስልክና በቦታውም በመገኘት ባሰባሰቡት መረጃ ሕወሓት ለሕዝቡ ምንም አይነት እርዳታ እያደረሰ አለመሆኑን ተገንዝበናል ብለዋል። ይልቁንም እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በላይ የሆኑ ልጆችን ወደ ውትድርና እንዲገቡ እናቶችንና አባቶችን ልጃችሁን አምጡ፤ ገንዘብ አምጡ በማለት እያሰቃየ ነው።

በቅርቡ ከመቀሌ የመጡትን የአይደር ሆስፒታል ሠራተኛ የሆኑትን ዶክተር አረጋዊ ሓጎስን እንዳናገሯቸውና ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው ሁለንተናዊ የግፍ ተግባር ለመስማት የሚቀፍ እንደሆነ ማረጋገጣቸውን ገልጸዋል።

በትግራይ ሕዝብ ስም የሚገባ እርዳታ ለሕዝቡ እየደረሰ አይደለም። ለአብነትም የሚላኩ መድኃኒቶችና ሌሎች የሕክምና ቁሳቁሶች ለሆስፒታሎች ሳይሆን ሕወሓት ባደራጃቸው መደቦች ስም በርካታ ፋርማሲዎች ተከፍተው አሸባሪ ቡድኑና ግብረ አበሮቹ እየበለጸጉበት መሆኑን መረዳት መቻላቸውን አቶ ሙሉ ብርሃን ጠቅሰዋል።

የትግራይ ሕዝብና ራሱን የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ብሎ የሰየመው አሸባሪው ሕውሓት አብረው መኖር የማይችሉ ናቸው ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ የሕወሓት መኖር በትግራይ ሕዝብ መጥፋት ላይ የተመሠረተ ነውም ብለዋል።

አሸባሪ ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ የሚያጠፉ፣ የሚጨቁን፣ የሚረግጥ ኃይል እንዳለ ሰፊ ፕሮፖጋንዳ በመሥራት እንዲደናገር አድርጎታል ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ ከሕዝቡ ባሻገር ዓለም አቀፍን ማኅበረሰብ እንዲደናገር አድርጓል ብለዋል።

ሕወሓት የራሱን እኩይ ተግባር ገልብጦ በማውራት የዓለምን ማኅበረሰብ እንዲደናገር ማድረጉን ያስታወሱት አቶ ሙሉብርሃን፤ ትዴፓ እውነታውን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማሳወቅ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በትግራይ ሕዝብ እየደረሰ ላለው መከራ መነሻውና መድረሻው ሕወሓት መሆኑን የገለጹት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ ሕወሓታዊ አስተሳሰብ እስካልጠፋ ድረስ የትግራይ ሕዝብ ሁለንተናዊ መከራ መቋጫ አያገኝም። ስለዚህ ለትግራይ ሕዝብ መከራ ትክክለኛ ተቆርቋሪ የሆኑ የክልሉ ተወላጅ ልሂቃን ድምጽ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

# ‹‹ሃገራዊ ምክክሩን...

ከገፅ 1 የዞረ

እንደ አቶ አባተ ገለጻ፤ ሰላም ሌሎች የዳር ተመልካች ሆነው በመንግሥት አካል ብቻ የሚረጋገጥ ጉዳይ አይደለም። ሰላም የሁሉም ድምር ውጤት ነው። አሁን የሚስተዋሉ የሰላም ችግሮች በአግባቡ ካልተቀረፉ ሃገሪቱ ወደ ማትወጣው ቀውስ ሊወስዱ ይችላሉ። ስለሆነም ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

አሁን በሃገሪቱ እንደሚታየው የጠለቀ ቁርሾና ጥላቻ በሕዝቡ መካከል እንደሌለ የገለጹት አቶ አባተ፤ የጥቂት ፖለቲከኞችና ምሁራን ነን ባዮች ሴራ ለችግሮቹ መደራረብ ምክንያት መሆኑን አንስተዋል።

ግጭት ተፈጠረ፣ ሰው ተገደለ፣ ሕዝብ ተፈናቀለ፣ንብረት ወደመ የሚሉ ወሬ ላለመስማት ሁሉም የሰላም ዘብ መሆኑ ወሳኝ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ግጭትና ጥፋት ለማርገብ የሚፈጥኑ አካላትም ፊታቸውን ለሰላምና መልካም ወደ ሆኑ ማኅበራዊ መስተጋብሮች ሊያዞሩ ይገባል ብለዋል።

በኅብረተሰቡ ዘንድ መረጃን የመምረጥና ለይቶ የመጠቀም ልምድን ማሳደግም አስፈላጊ መሆኑን አመልክተዋል።

ያለ ሰላም ሃገር ትርጉም አልባ መሆኗን በአንድ ወቅት የተከበሩ የነበሩ በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ የምንመለከታቸውን ሶሪያውያንን ማየት በቂ ነው ያሉት አቶ አባተ፤ ከዚህ አንጻር የሃይማኖት አባቶች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ አባ ገዳዎች፣ ፖለቲከኞችና ምሑራንም ሕዝቡን ለማቀራረብ በጋራ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

ሃገራዊ ምክክር ኮሚሽኑም ጥያቄ ያለው ሁሉ የጠብመንጃ አፈሙዙን በማዘቅዘቅ ጥያቄውን ይዞ ለምክክር እንዲቀርብ ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

እንደ አቶ አባተ ገለጻ፤ አሁን ላይ የመተሳሰብ ሁኔታ በሚፈለገው ቁመና ላይ ባለመሆኑ ለተቸገሩ ወገኖች የሚደረገው ድጋፍም በአንድ ወገን ብቻ ከመሆን አልፎ ሕዝባዊ መሠረት ሊኖረው ይገባል።

እንደ ሃገር የቆየውን ሕዝባዊ ትስስር ለማጠናከር በተረጋጉ አካባቢዎች የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች እንዲጎበኙ ማድረግ የሌላውን ችግር እንዲገነዘቡ ማድረግ የወገናዊነትን ስሜት ያጠናክራል። በተለይ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ለችግር የተጋለጡና በድርቅ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸዉን ወገኖች ድጋፍ ማድረግ ሊፈጥር የሚችለው መስተጋብር ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መገናኛ ብዙኃን ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የማይተካ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል!

መገናኛ ብዙኃን ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ሚዛናዊና ወቅታዊ መረጃዎችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የማይተካ ሚና አላቸው። ይህ ሚናቸው ደግሞ አገራዊ በሆኑ የጋራ አጀንዳዎች ላይ በእጅጉ ሊፈተን ወይም ከፍ ብሎ ሊገለጥ የሚችልበት እድል አለ። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን በአዎንታዊም፤ በአሉታዊም የሚነሱባቸው ነገሮች አሉ። ይህ ምናልባት እንደ መገናኛ ብዙኃኑ ተቋማት ግብና ዓላማ፤ ካልሆነም እንደየተመልካች፣ አድማጭና አንባቢዎቻቸው ምልከታ ሊለያይ፤ አንዱ በአዎንታዊ የሚያነሳው ለሌላው አሉታዊ ሊሆን መቻሉ እሙን ነው።

ይህ የማንነታቸው ገጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን፤ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ ላለችበትም ሆነ ወደፊት እንድትሆን ከሚታሰበው ራዕይ አኳያ የመገናኛ ብዙኃን ሚና ተኪ የሌለው መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም። ምክንያቱም በእስካሁኑ የአገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ውስጥ በአዎንታዊውም ሆነ በአሉታዊ ገጹ የሚተረከው የመገናኛ ብዙኃን ሚና እንዳለ ሁሉ፤ በቀጣይ ኢትዮጵያን ከፍ ወዳለ ሁሉን አቀፍ ብልጽግና በማስጓዝ ሂደቱ ውስጥ ሚናቸው በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ እንዲገለጽ የማድረግ እድሉ በእጃቸው ነው።

ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ከትናንት ሲንከባለሉ የመጡና በአገር ግንባታ ሂደቱ ላይ የራሳቸውን እክል የሚፈጥሩ ጉዳዮችን በምክክርና ውይይት ለመፍታት ከፍ ያለ ሥራ ጀምራለች። አገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሕግ በማቋቋምና ኮሚሽነሮችን በመሰየምም ወደ ሥራ ተገብቷል። ሂደቱም የተሳለጠ እንዲሆን ከባለድርሻ አካላት ጋር ሰፋ ያሉ ውይይቶች እየተደረጉ ሲሆን፤ ዋናውን የምክክር ሂደት ለመጀመር የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ተግባራትም በመከናወን ላይ ናቸው። እነዚህን ሁነቶች እየዘገቡ ለሕዝብ ጆሮ እያደረሱ ያሉት ደግሞ የመገናኛ ብዙኃን ናቸው።

የመገናኛ ብዙኃኑ አገራዊ የምክክር ሂደቱንና ክንውኑን በተመለከተ ሁነትን ከመዘገብ የዘለለ ከፍ ያለ ሚና አላቸው። ምክንያቱም የምክክር መድረኩ ከፍ ያለ ሃሳብ የሚደመጥበት፣ ከፍ ያለ ክርክር የሚደረግበት፣ ከፍ ያሉ የመፍትሔ ሃሳቦች የሚፈልቁበት፣ ከፍ ያሉ የአገር ግንባታ ሥራ አቅጣጫዎች የሚመላከቱበት፣ በጥቅሉ ትልቋን ኢትዮጵያ እውን በማድረግ ሂደት ውስጥ መላው ኢትዮጵያውያን የጋራ ጉዳይ ኖሯቸው የጋራ አገራቸውን በጋራ የሚገነቡበትን እድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ታላላቅ እውቀቶች የሚፈልቁበት በመሆኑ ነው።

እነዚህ ታላላቅ እውቀቶች ከተለያየ አቅጣጫ፣ በተለያየ አመለካከት፣ በተለያየ አገላለጽ፣ በተለያየ ስሜት፣ በተለያየ ማንነት፣ በተለያየ የእድሜና የትምህርት ደረጃ፣ እንዲሁም በተለያየ ፍላጎትና ሁነት ውስጥ ሊነገሩና ሊቀርቡ ይችላሉ። የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ግን ልዩነትን ማስፋት ሳይሆን ማጥበብ፤ ችግሮችን ማወሳሰብና ማግዘፍ ሳይሆን፣ ችግሮችን በእውቀትና ብልሃት ላይ ተመሥርቶ መፍታት፤ ለመወቃቀስና ለበቀል ሳይሆን፣ በትናንት ስህተቶች ላይ ተነጋግሮ በይቅርታ ለመሻገር፤ የልዩነት ምንጭ የሆኑ ጉዳዮችን ወደፊት በማምጣትና በመነጋገር ቢያንስ የጋራ የሆኑ ጉዳዮችና አጀንዳዎች በሚባሉት ላይ መግባባትን መፍጠር፤ ወዘተ. እንዲቻል ማድረግ ነው።

ይህ እንዲሆን ደግሞ ሃሳቦች በነጻነት እንዲንሸራሸሩ በማድረግ ረገድ የመገናኛ ብዙኃን ዋናዎቹ ተዋናዮች ይጠበቅባቸዋል። ዛሬን የሕዝብ ፍላጎትና ስሜትን ከማንጸባረቅ አኳያ ውጤታማ እንዲሆኑ የትናንት ችግሮቻቸውን ለይተው፤ ከቡድንና አካባቢያዊ ልሳንነት ይልቅ የሁሉም ድምጽ ሆነው፤ የጎጥ ጥቅምን ለማስጠበቅ መሣሪያ ከመሆን ወጥተው አገርን አስቀድመው ስለ አገር ክብርና ከፍታ እያሰቡ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህ ሥራቸው ደግሞ ራሳቸውን ገለልተኛ ማድረግ እና ለየትኛውም ቡድን ፍላጎት መሳካት ከሚደረግ ጥረት ነጻ ማውጣት ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ የክልል መገናኛ ብዙኃንን ብንወስድ፤ የክልል ሚዲያ ስለሆኑ ራሳቸውን ካሉበት ክልል እሳቤ ጋር ብቻ ማቆራኘት አይጠበቅባቸውም። ምክንያቱም ይሄን አይነት አካሄድ እስካሁን ተሞክሮ ፉክክርን እንጂ ትብብርን ሲያሰፍን አልታየምና። በመሆኑም ከክልል እሳቤ ከፍ ብለው አገራዊ ስዕልን ይጎናጸፉ ያስፈልጋል። ይሄን ለማሳያነት ለማንሳት ተሞከረ እንጂ የመገናኛ ብዙኃን እንደ ቆሙለት ዓላማ፣ በባለቤትነት እንደያዛቸው አካልና ሌላም ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ዘርን፣ አካባቢን፣ ሃይማኖትን ወይም ሌላ ቡድናዊ እሳቤን ተከትሎ የመንጎድ አዝማሚያዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

በተመሳሳይ አገራዊ ምክክሩ ከዳር እንዲደርስ የማይፈልጉ ውጫዊም ውስጣዊም የአገር ጠላቶች እና በሕዝብ አምካኝ አስተሳሰቦች ሊጠለፉ የሚችሉበት እድል ሊፈጠር ይችላል። ይህ ሲሆን ደግሞ ከአንድነት ይልቅ የልዩነት ሃሳቦችን፤ ከመደማመጥ ይልቅ የመጠላለፍ ሂደቶችን፤ ከመተማመን ይልቅ የመጠራጠር ዕሳቤዎች፤ ከመግባባት ይልቅ የተቃርኖ አጀንዳዎችን፤ በጥቅሉ ከሰላም ይልቅ መነታረክና ግጭትን በሚያጠነጥኑ ነጥቦች ላይ በማተኮር የምክክር ሂደቱ አቅጣጫውን እንዲስት የማድረግ አቅማቸው ከፍ ያለ ሊሆን እንደሚችልም መዘንጋት አይገባም።

ይህ እንዳይሆን ደግሞ መገናኛ ብዙኃን ስለ አገራዊ የምክክር መድረኩ ስኬታማነት ከወዲሁ ምን፣ እንዴትና በምን አግባብ መሥራት አለብኝ? የሚለውን ጉዳይ አጢነውና ለይተው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ይሄን ሲያደርጉ የቡድኖች ሳይሆን የሃሳቦች መድረክ በመሆን ታላቋን አገር እውን በማድረግ ሂደት ውስጥ ተግባብተውና ተባብረው የሚሠሩ ሕዝቦችን መፍጠር ይችላሉ። የመገናኛ ብዙኃን ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የማይተካ ሚናቸውን ሊወጡ የሚገባውም ይህ እውን እንዲሆን ነው!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ትኩረት የሚያሻው ምግብን ከባዕድ ነገሮች የመደባለቅ ወንጀል

መላኩ ኤሮሴ

ነጋዴዎች በትንሽ ድካም ብዙ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ የሚፈጽሟቸው አሻጥሮች በአገሪቱ ውስጥ ለሚስተዋለው የዋጋ ግሽበት፣ የመሠረታዊ የእቃና አገልግሎት ዋጋ ንረት እና እጥረት፣ የውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ የኑሮ ውድነት እና የመሳሰሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንዱ መንስኤ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ። በነጋዴዎች ከሚፈጸሙ አሻጥሮች መካከል ምግብና ምግብ ነክ ምርቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ መሸጥ አንዱ ነው።

ምግብን እና ምግብ ነክ ምርቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር በመደባለቅ ነጋዴዎች ትርፍ ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት በእኛ ዘመን የተጀመረ እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ከጥንት ስልጣኔዎች ዘመን ጀምሮ ወይንን ከውሃ፣ እንዲሁም ወተትን ከውሃ ጋር በመቀላቀል ነጋዴዎች በትንሽ ወጪ ብዙ ትርፍ ለማግኘት ጥረት ያደርጉ እንደነበር መዛግብት ያስረዳሉ።

በእርግጥ በጥንት ዘመን ነጋዴዎች ትርፍን ለማግኘት በምግብ እና ምግብ ነክ ምርቶች ላይ የሚቀላቅሏቸው ነገሮች ነጋዴዎቹ ትርፍ እንዲያገኙ ከማስቻል በዘለለ በዘመናችን እንደሚስተዋለው በሸማቾች ጤና ላይ ቀውስ የማስከተል እድላቸው አነስተኛ ነው።

በአገራችን በዋናነት የምርት ክለሳ ወይም ለጤና ጠንቅ የሆኑ ባዕድ ነገሮች መቀላቀል የሚታይባቸው ምርቶች ቅቤ፣ በርበሬ፣ ወተት፣ አይብ፣ ማር፣ ዱቄት፣ ቡና፣ ዘይት እና እንጀራ መሆናቸው በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ካወጣቸው መግለጫዎች መረዳት ይቻላል።

እንጀራ ከጀሶ፣ ቅቤ ከሙዝ፣ ማር ከሞላሰስ ወይም ከስኳር፣ በርበሬ ከሸክላ አፈር እና ከቀለም፣ ጤፍን ከአሸዋ፣ ቡናን ከዋንዛ ፍሬ ጋር የሚቀላቅሉ ነጋዴዎችን አስመልክቶ የአገራችንን ሚዲያዎች ዘገባ መስማት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተለመደ ዘገባ ሆኗል።

ምግብ እና ምግብ ነክ ምርቶች ላይ ባዕድ ነገሮችን መቀላቀል በኢኮኖሚ ላይ ከሚፈጥረው ችግር ባሻገር የዜጎች ጤና ላይ ከባድ ችግር ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ከሌሎች የኢኮኖሚ አሻጥሮች በላይ እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል። ከባዕድ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉ ምግቦች እንደ ካንሰር፣ ኮሌስትሮል፣ ኩላሊት፣ ደም ግፊትና የመሳሰሉ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች መንስኤ እየሆነ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ። ለዚህም ነው በምግብ ላይ ባዕድ ነገሮችን የመቀላቀል ወንጀሎችን ለመከላከል የተለየ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው።

> **ምግብ እና ምግብ ነክ ምርቶች ላይ ባዕድ ነገሮችን መቀላቀል በኢኮኖሚ ላይ ከሚፈጥረው ችግር ባሻገር የዜጎች ጤና ላይ ከባድ ችግር ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ከሌሎች የኢኮኖሚ አሻጥሮች በላይ እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል። ከባዕድ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉ ምግቦች እንደ ካንሰር፣ ኮሌስትሮል፣ ኩላሊት፣ ደም ግፊትና የመሳሰሉ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች መንስኤ እየሆነ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ። ለዚህም ነው በምግብ ላይ ባዕድ ነገሮችን የመቀላቀል ወንጀሎችን ለመከላከል የተለየ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው**

እንደዚህ አይነት ምግብ እና ምግብ ነክ ምርቶችን ከባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ መሸጥ በተለይም በበዓላት ወቅት የመባባስ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። የበዓል ወቅት ምርቶች በገፍ ወደ ገበያ የሚቀርቡበት ወቅት እንደመሆኑ ለመንግሥት አካላት ለቁጥጥር አዳጋች ስለሚሆን እኩይ ዓላማ አንግበው ለሚንቀሳቀሱት የበለጠ በር ሊከፍት ይችላል።

ይህ ከሕግ አንጻርም ሆነ ከሞራል አንጻር ትክክል ያልሆነ ተግባር እንደመሆኑ ማንም ሳያስገድዳቸው ነጋዴዎች ከእንደዚህ አይነት ተግባር ሊቆጠቡ ይገባል። የዜጎችን ጤና የሚጎዳ ተግባር በመፈጸም የሚገኝ ኢኮኖሚያዊ ትርፍ ዘላቂ ትርፍ ሊሆን አይችልም። ወንድምና እና እህት ኢትዮጵያውያንን ጤና በማወክ የሚገኘውን የትኛውንም አይነት ትርፍ ሊጠየፉ ይገባል።

ሁሉም ነጋዴ በሕግ እና በሞራል ላይመራ ይችላል። ሕግና ሞራል የማይገዛቸው ነጋዴዎችን ሕዝቡ ሊያጋልጣቸው ይገባል። ምግብ የሚመስሉ ነገር ግን የምግብነት ይዘት የሌላቸው ምርቶች ከምግብ ጋር መቀላቀል ለሰው ልጆች የጤና እክል ከማስከተላቸው ባሻገር ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዛቸው የከፋ እንደመሆኑ ይህንን ችግር ለመከላከል ሕዝቡ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅርበት መሥራት አለበት። ለሕግ አካላት እና ለሸማች ማኅበራት ጥቆማ በመስጠት ምርቱ እንዲወገድ ወይም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድበት ሊሠራ ይገባል።

ሕዝቡ የሚያቀርባቸውን ጥቆማዎች በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በትኩረት ሊሰሩ ይገባል። ምግብ እና ምግብ ነክ ምርቶች ላይ ባዕድ ነገሮችን መቀላቀልን ለመከላከል ከዚህ ቀደም የወጡ የተለያዩ አዋጆች አሉ። እነዚህን አዋጆች በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

ከዚህም ባለፈ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያሉ አዋጆች እና ሕጎችን መፈተሽ ያስፈልጋል። አዋጆቹና ሕጎቹ ክፍተት ካለባቸው ክፍተቶቹን መሙላት ለነገ የማይባል ተግባር ሊሆን ይገባል። በአሁኑ ወቅት ሥራ ላይ ካሉ አዋጆች ባሻገር በዚህ ተግባር ላይ የሚሳተፉ ነጋዴዎች ላይ አስተማሪ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ ተጨማሪ የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

በቀጣይ ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ ባዕድ ነገሮች የተቀላቀለባቸው ምርቶችን ለመለየት የሚያስችሉ ላቦራቶሪዎችን ማጠናከር ልዩ ትኩረት የሚያሻው ነው። ለዚህ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ይህንን ተግባር እየሠራ ያለው የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አቅም ማጠናከር ወሳኝነት አለው።

ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ ከሚደረጉ ጥረቶች ባሻገር በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሩን ለመቀነስ ፖሊስ በትኩረት ሊሠራ ይገባል። ምግቦች ከባዕድ ነገሮች ጋር ሲደባለቁ በቀጥተኛ እማኝ ሊሆኑ የሚችሉ የሰዎችና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ ፖሊሳዊ ኦፕሬሽኖችን መሥራት ይገባል። በመሰል እኩይ ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላት ላይ ሕጋዊና አስተማሪ እርምጃዎች ሊወሰድባቸው ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ

# ትልቅ ተስፋ - ለትልቅ አገርና ሕዝብ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ስለ ተስፋ እነግራችኋለሁ:: ተስፋ ስላችሁ ግን በምንምነት ውስጥ ያለውን ህልም እልም ዓይነቱን ተስፋ እያልኳችሁ አይደለም:: በራዕይ ውስጥ ስላለው፣ ለለውጥ በተነሱ ልቦች ውስጥ ያለውን እሱን ማለቴ ነው:: ትልቅነት መብቀያው በአንድ ሀሳብ በተስማሙ ልቦች ውስጥ ነው:: ኢትዮጵያ አገራችን የአንድነት ተስፋ ርቋት ለዘመናት ኖራለች:: አሁን እነዛን ተስፋ ማጣቶች በተስፋ የምናድስበት ሰሞን ላይ ነን:: የተስፋ ወደብ ፍቅር ነው:: ፀሐይ በምሥራቅ በኩል ብልጭ እንደምትል ሁሉ የአገርም ተስፋ በምክረ ሀሳብ ውስጥ ፍሬ የሚያፈራ ነው:: ያጣናቸው እነዛ ትናንትናዊ ጣፋጭ ፍሬዎች በአንድነትና በፍቅር ማጣት የደረቁ ናቸው:: በወንድማማቾች ጥል የጎመዘዙ ናቸው:: ትልቅ አገር እንዲኖረን ከሁሉም በፊት በትልቅ ልብ ውስጥ የተጻፈ ትልቅ ተስፋ ሊኖረን ይገባል:: ትልቅ ልብ ነውር አያውቅም:: የእስከዛሬ ነውራችን በትንሽ ልብና በትንሽ ሀሳቦቻችን የፈጠርናቸው ናቸው:: ችግሮቻችንን ቁጭት በወለደው የኅብረብሔራዊነት ተስፋ መግደል አለብን::

የቆማችሁት በምን ይመስላችኋል? ወጥታችሁ የምትገቡት በምን ኃይል በምን ብርታት ቢሆን ነው? እዚህ ዓለም ላይ በሕይወት ለመኖር እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ኃይሎች ውስጥ አንዱ የተስፋ ኃይል ነው:: የተስፋ ኃይል ደግሞ በአንድነትና በወንድማማችነት የተቃኘ ኃይል ነው:: አገር ተስፋ ያለው ወጣት፣ ተስፋ ያለው ዜጋ፣ ተስፋ ያለው መሪ በአጠቃላይ ተስፋ ያለው ትውልድ ያስፈልጋታል:: ይሄ የሚሆነው ደግሞ በጋራ መስራትን፣ በጋራ ማሰብን ባህል ስናደርግ ነው:: ሕይወት ከተሠራችባቸው ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ አምላካዊ ቀመሮች ውስጥ ተስፋ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል:: በሃይማኖት አስተምህሮ ላይ እንኳን ተስፋ ለሕይወት ያለውን የላቀ ዋጋ ማየት እንችላለን:: ተስፋውን የገደለ፣ ተስፋውን ያጣ ሰውነት ለመኖር አቅም አያገኝም:: ትልቁ መኖራችን ያለው በትልቁ ተስፋችን ውስጥ ነው::

እንደ አገር ወደ ፊት እንድንሄድ፣ ወደ ፊት እንድናይ ልባዊ ተስፋ ያስፈልገናል:: ያለ ሙልዕተ ተስፋ ምንም ነን:: ተስፋ በራዕይ ውስጥ ያለ ለለውጥና ለአዲስ ነገር በሚጓጓ መንፈስ ውስጥ የሚፈጠር የመልካም ነገሮች ፍኖት ነው:: ከግለሰባዊነት ባለፈ ለአንድ አገርና ሕዝብ ያለው ሁለንተናዊ ፋይዳ እንዳለ ሆኖ እድገትና ስልጣኔ ከሚፈበረኩባቸው አእምሮአዊ የልማት ኃይል አንዱና ዋነኛው ነው ባይ ነኝ:: በተለይ እንደኛ አገር ባሉ በትናንት የውሸት ትርክት ዛሬን መኖር ያልቻሉ ሕዝቦች ባሉበት አገር ላይ ትናንትን የሚሽር ሁሉን አቀፍ አገራዊ ተስፋ ግድ ይላል:: መኖር መተንፈስ ብቻ አይደለም፣ መኖር መተንፈስ ብቻ ነው ብንል እንኳን እንድንተነፍስ የሚያበረቱን ኃይሎች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም:: እንድንኖር፣ እንድንተነፍስ አቅምን ከሚፈጥሩልን ኃይሎች ውስጥ አንዱ ጸዐዳ ተስፋ ነው::

ተስፋ ከስኬትና የምንፈልገውን እንድናገኝ ከማድረግ ባለፈ እንዳንሞት የሚያደርግ ታላቅ ሰውነታዊ ኃይል አለው:: ሰዎች ሁሉ የሚወድቁት፣ ሰዎች ሁሉ የሚሞቱት ተስፋ ሲያጡ እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: በሕክምናው ዓለም ብናይ እንኳን የአንድ ህመምተኛ የመዳንና የመሞት ልኬት የሚወሰነው በተስፋ ነው:: ተስፋ አለው..ተስፋ የለውም ሲባል ሰምታችኋል ብዬ አስባለሁ:: ተስፋ በመኖርና በመሞት መካከል የተሰመረ የህላዊ ድንበር ነው:: በተስፋ ማጣት ውስጥ ሆነን የምናሳካው ህልም፣ የምናሳካው ራዕይ የለም:: በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነን የምንማረው ትምህርት፣ የምንይዘው ትዳር በአጠቃላይ የምንኖረው ሕይወት ዋጋ ቢስ ነው:: ለምንም ነገር በተስፋ የተሞላ ልብና መንፈስ ያስፈልገናል:: ለምንም ነገር ወደፊት ሊያስኬደን የሚችል ብርቱ መነቃቃት ግድ ይለናል:: አሁን ላይ እንደ አገር ተስፋ ያስፈልገናል:: ከዛሬ የተሻለ ነገን የማየት፣ ከትናንት የበረታ ዛሬን የመኖር ተስፋ ያስፈልገናል:: ተስፋ ዝም ብሎ አይፈጠርም..ተስፋ ከአንድነትና ከአብሮነት የሚነሳ መድረሻውንም አገርና ሕዝብ ያደረገ ኃይል ነው:: እየተገፋፋን፣ እየተናቆርን ከዛሬ አርቀን ማየት አንችልም:: እንደ አገር ለጋራ ጥቅም የሚታትሩ አእምሮና ልብ ሳንገነባ ወደ ፊት ፈቀቅ ማለት አይቻለንም::

በሕይወት ውስጥ በእያንዳንዱ ነገራችን ላይ ግፍና ጸዐዳ መልኩን ይዞ ተስፋ አብሮን አለ:: ዛሬ ላይ በብዙ ችግርና ማጣት የምንሰቃየው ውስጣችን ተስፋ ባለመኖሩ ነው:: ወይም ደግሞ ሳንሠራና ሳንለፋ በአጉል ተስፋ በመጠበቅ ውስጥ ስለቆምን ነው:: በነገራችን ሁለት ዓይነት ተስፋዎች አሉ:: አንደኛው የበረከት..የልዕልና ተስፋ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የማጣት..የድህነትና የእኩይ ነገሮች ተስፋ ነው:: አሁን ላይ ብዙዎቻችን በሁለተኛው የተስፋ ጎዳና ላይ የቆምን ነን:: ሁለተኛው ተስፋ ማለትም የድህነትና የማጣት ተስፋ ያልኳችሁ ውስጣችን ምንም ዓይነት ራዕይና መነሳሳት ሳይኖር በስሜት..በደመነፍስ እንዳው ዝም ብለን ከመሬት ተነስተን በብዙ ልፋት የሚገኝን አንድን ነገር የእኛ እንዲሆን መጠበቅ ማለት ነው:: ይሄ የተስፋ ዓይነት ሰዎችን ከመጉዳትና እኔ ከንቱና የማልረባ ነኝ፣ ለመልካም ነገር አልተፈጠርኩም ብለን ራሳችንን እንድንጠላ ከማድረግ ባለፈ የሚጠቅመን አንዳች ነገር የለም:: በዚህ የተስፋ ዓይነት ውስጥ መኖር ጉዳቱ ይሄ ብቻ አይደለም በሕይወት ውስጥ ለብዙ ግራ መጋባትና ለብዙ ያልተገቡ እኩይ አመለካከቶች በመዳረግ አቅማችንን በመግደል ለሱስና ለመሰል አላስፈላጊ ድርጊቶች እንድንጋለጥ በር ይከፍትብናል::

ዛሬ ላይ ብዙ ህልማችን ብዙ ራዕዮቻችን የመከኑብን በዚህ የሞት ተስፋ ላይ ስለቆምን ነው:: እውቀትና ጉልበት ይዘን ከንቱ ሆነን የምንኖረው በዚህ የውሸት ተስፋ ላይ ስለተደገፍን ነው:: አገርና ሕዝብ ከመጥቀም ይልቅ የወጣት ጡረተኛ ሆነን ከአያቶቻችን እጅ ላይ የምንበላውም በዚህ የተነሳ ነው:: በተስፋ ለመኖር እንዴት ተስፋ ማድረግ እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል:: በነገራችን ላይ ይህ የተስፋ ዓይነት የሞት ተስፋም ሊባል ይችላል:: በሕይወታችን የመጨረሻው ክፉ ነገር ላይ የምንደርሰው በዚህ ተስፋ ውስጥ አልፈን ነው:: በዚህ ተስፋ ውስጥ ለውጥ የለም፣ በዚህ ተስፋ ውስጥ ደስታ የለም:: እርሱ ሕይወታችን የሚባክንበት፣ ህልም ራዕያችን የሚመክንበት የውድቀት ጥግ ነው:: ብዙዎቻችን ባለመንቃት ባለማሰብና ባለማወቅ ምርጡን የተስፋ ዓይነት ትተን በዚህ የሞት ተስፋ ውስጥ እንኖራለን:: እናም አሁኑኑ ያለንበትን የተስፋ ሁኔታ ዞር ብለን ማየቱ ጥሩ ነው:: ያለዛ እየባከንን ነው:: ምንም ጥሩ ነገር ላንፈጥር የማይመጣን፣ የማይሆንን ነገር እየጠበቅንነው::

ሁለተኛው የተስፋ ዓይነት የምርጦች ተስፋ ይባላል:: ምክንያቱም ምርጥ ነገር ሁሉ ለምርጥ ጭንቅላት የተቀመጠ ስለሆነ ነው የምርጦች ተስፋ ያልኩት:: በዚህ የተስፋ ዓይነት ውስጥ ሞትና ርኩሰት የለም:: በዚህ የተስፋ ዓይነት ውስጥ መውደቅ የለም:: ብንወድቅ እንኳን እንድንነሳ የሚያስችል ኃይል ይኖረናል:: በዚህ የተስፋ ዓይነት ውስጥ አሁን ላይ ብዙ ነገራችን ልክ እየመጣ ነው እላለሁ:: ደስታችን፣ ሰላማችን እንዲሆንልን የምንፈልገው ነገር ሁሉ በዚህ የተስፋ ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ነው:: በወጣትነታችን በጎ ሥራ እየሠራን ያለን ሁሉ፣ በሥራችን ስኬታማ የሆንን ሁሉ፣ በምንፈልገው ነገር ላይ ውጤታማ የሆንን ሁሉ ውስጣችን በገነባነው የለውጥ ተስፋ ላይ ስለቆምን ነው:: እንደ ዜጋ ለአገራችን መልካም ከሠራን፣ እንደ መንግሥት፣ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ተነጋግሮ መግባባትን ካስቀደምን በምርጥ ተስፋ ስር ነን ማለት ነው:: ምርጥነት ከማሰብ ይጀምራል:: የሚያስብ ጭንቅላት ተስፋ የሚያደርገው ነገር ይኖራል:: በማሰብና ተስፋ በማድረግ ውስጥ ደግሞ ራዕይና ህልም እውን ይሆናል ማለት ነው::

ብዙዎቻችን ሳናስብ ተስፋ የምናደርግ ነን:: ሳናስተውል ተስፋ ያደረግነው ነገር ደግሞ ከመሆን ይልቅ ላለመሆን የቀረበ ነው:: ምክንያቱም ሁሉም ነገር ማስብን ስለሚፈልግ ነው:: ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት ማሰብ ይቀድማል:: እስካሁን ድረስ የተበላሹ ሕይወታዊ አጋጣሚዎች ሁሉ ካለማሰብ በቀቢጸ ተስፋ የተከወኑ ስለሆኑ ነው::እንደ አገር የጋራ ተስፋ ቢኖረን ኖሮ አሁን ላይ በችግሮቻችን ላይ ተነጋግሮ መግባባት ባልከበደን ነበር:: የአገራዊ ምክክሩ ዋና አላማ እኮ ተስፋን መፍጠር ነው:: በተግባቦት አንድነትን ማምጣት ነው:: ተስፋ የሚፈጠረው ደግሞ በእርቅና በውይይት ነው:: የጋራ ተስፋን ለመፍጠር የጋራ ውይይት የጋራ እርቅ ያስፈልገናል:: ይሄ ባልሆነበት ሁኔታ ላይ የምንፈጥረው ተዐምር አይኖርም:: ሁሌም ወደ ትልቅ ነጋችን..ወደምንፈልገው የከፍታ ምዕራፍ ለመሸጋገር በማሰብ የታገዘውን፣ በመነጋገር የተቃኘውን እኛን መፍጠር ይኖርብናል:: እግር የሚራመደው በማሰብ ነው:: እጅ የሚሠራው፣ አይን የሚያየው፣ ጆሮ የሚሰማው ሁሉ ነገራችን ጥቅም እየሰጠን የሚገኘው ከማሰብ ቀጥሎ ነው:: አንዳንድ ሰዎች አሉ፤ ከቤት ይወጡና ወዴት እንደሚሄዱ የማያውቁ:: የት ነው የምትሄዱት ተብለው ሲጠየቁ ወዴት እንደምሄድ አላውቀውም ዝም ብዬ ነው የምራመደው የሚሉ::

ካለማሰብ፣ ገበያ ስለሆነ ብቻ ገበያ የምንሄድ እኮ አለን:: ካለማስተዋል፣ በለው ሲባል ሰምተን በለው እያልን የምንጮኽ ሞልተናል:: ካለመረዳት ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያየነውን ውሸት እውነት ነው ብለን ለሌሎች አጋርተን እናውቃለን:: የጋራ ተስፋ አጥተን በልዩነቶቻችን ላይ ጊዜ የምናጠፋ አለን:: ይሄ ሁሉ መቀየር አለበት:: በትልቅ ተስፋ ትልቅ አገርና ሕዝብ መገንባት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል:: ሕይወት ማሰብ ናት፤ ካለማሰብ የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ጉዳት ነው ይዘውብን የሚመጡት:: ላለመግባባት ብንወያይ፣ ላለመስማማት ስብሰባ ብንቀመጥ የምናተርፈው ትርፍ የለም:: ተነጋግረን መግባባት ካልቻልን፣ በአንድ የሚያቆመን የጋራ ተስፋ ከሌለን ለራሳችንም ሆነ ለአገራችን ውለታ መዋል አንችልም:: ይሄ ሆነ ማለት ደግሞ ትልቁ ተስፋ ከእኛ ጋር አይደለም ማለት ነው፤ ወይም ደግሞ በሕይወት ውስጥ የምንለፋለት፣ ማለዳ..በየቀኑ አብዝተን የምናስበው የስኬት ጫፍ የለንም ማለት ነው:: ትልቅ ተስፋ ውስጣቸው ያለ ሰዎች ከአገር የሚበልጥባቸው ምንም ነገር የለም:: ለውይይት፣ ለእርቅ የሚሆን ብዙ አቅም፣ ብዙ ችሎታ አላቸው::

ውሳኔያችንን ለእግሮቻችን ሳይሆን ለአእምሯችን እንተውለት፡ ዓይኖቻችን መልካም እንዲያዩ፣ ጆሮዎቻችን መልካም እንዲሰሙ ራሳችንን በመልካምና በሚገባ ቦታ ላይ እናቁመው:: ምርጥ ነገሮች ሁሉ በምርጥ ተስፋዎች ውስጥ የተቀመጡ ናቸው:: አሁን ላይ በእውቀታቸው፣ በጉልበታቸው በገንዘብና በጊዜአቸው አገርና ሕዝብ እያገለገሉ ያሉ እነሱ በምርጥ ተስፋ ውስጥ የሚኖሩ የምርጥ ተስፋ ውጤቶች ናቸው:: ትልቅነታችን ያለው በዚህ ትልቅ ተስፋ ውስጥ ነው:: ተስፋ የሌለው ትውልድ ተስፋ የሌለው አገርና ሕዝብ የመፍጠር ኃይል አለው:: ተስፋችን ለእኛ ብቻ ሳይሆን ከእኛ ቀጥሎ ለሚመጣው አዲሱ ትውልድም የላቀ ዋጋ አለውና አገርና ሕዝብን ወደ ፊት ሊያራምድ የሚችልን ትልቅ በጣም ትልቅ ተስፋን የእኛ ማድረግ ይኖርብናል:: በሕይወት ውስጥ የብዙ ነገር መጨረሻዎች ከተስፋ ብዛትና ከተስፋ ማጣት የሚመጡ ናቸው::

እንዳልኳችሁ ትላልቅ ተስፋዎች ትላልቅ ሰዎችን የመፍጠር ኃይል አላቸው:: በትላልቅ ተስፋ የተፈጠሩ ትላልቅ ሰዎች ደግሞ በአካል፣ በአእምሮ፣ በሥነ ልቦናና በኢኮኖሚ አቅማቸው የተገነቡ ናቸው:: እኚህ ግለሰቦች ለአገር የሚሆን ብዙ ነገር ይኖራቸዋል:: እኚህ ግለሰቦች ችግር ፈጣሪ ሳይሆኑ ችግር ፈቺ ናቸው:: በነዚህ ግለሰቦች የተፈጠረች አገር ደግሞ ከፍ ያለ ገጽታ ይኖራታል:: በትልቅ ተስፋ ውስጥ መኖር ራስን በትልቅ አገራዊ እውነት ውስጥ ማስቀመጥ ነው:: አሁን ላይ አገራችን ላለችበት ማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ቀውሶች ችግር ፈጣሪዎች ሳይሆኑ በእውቀትና በተስፋ የተካኑ ችግር ፈቺ ዜጎች ያስፈልጋሉ:: በእውቀት በሥልጣኔ የሚበልጡን ሰዎች በዙሪያችን መኖራቸው የላቀ ዋጋ አለው:: ከሚበልጡን ጋ ስንሆን እነሱን ለመሆን፣ የደረሱበት ለመድረስ እንበረታለን:: ትንሹን ተስፋችንን ገድለን ትልቁን ተስፋ ውስጣችን እንገነባለን:: በዚህም ብርቱና ታታሪ በመሆን አገር አሻጋሪ ከሆኑት ውስጥ እንመደባለን ማለት ነው::

በእወቀትም ሆነ ተስፋ በማድረግ ከእኛ ካነሱት ጋር ስንሆን ግን ራሳችንን ከማሻሻልና ከማበርታት ይልቅ በነበርንበት እንድንቆይ እንገደዳለን:: ስለዚህም በዙሪያችን በተስፋ የተለቁ በእውቀትና በጥበብ የተሻሉ ሰዎች ስለመኖራቸው እርግጠኛ መሆን ይጠበቅብናል:: ከሚበልጡን ሰዎች ጋር ወዳጅነትን ስንፈጥር ከነበርንበት አስተሳሰብ፣ ከነበርንበት ኋላ ቀር ሕይወት የመውጣት ዕድሎች ይኖሩናል:: ሁሌም ቢሆን ትንሹን ተስፋችንን ገድለን ወደ ትልቁ ለመሄድ ጉልበትና ኃይልን የሚፈጥሩልን ሰዎች ያስፈልጉናል:: ከተኛንበት የሚያነቃን ውስጣችን ትልቅ ተስፋ የለም ማለት ራሳችንን እያጣነው ነው ማለት ነው:: ተነጋግረን መግባባት ካልቻልን አገራችንን እያጣናት ነው ማለት ነው:: ይሄ እንዳይሆን አገር የሚገነባ፣ አገር የሚያቆም የጋራ ተስፋ ያስፈልገናል:: እንደ አገርም ሆነ እንደማኅበረሰብ አሁን ካለንበት የሕይወት ምስቅልቅል የምንወጣው በትልቅ ተስፋ ትልቅ ነገር ስንጀምር ነው::

ከምኞት ወጥተን ወደ ተጨበጠ ገሀዳዊ እውነት ለመሸጋገር ልዕለ ኃያል ተስፋ ያስፈልገናል:: ልዕለ ኃያል ተስፋ የሚገነባው በጠንካራ የሥራ ልምድ፣ ምንም ነገር እንደምንችልና እንደምናሳካ ማመን ስንጀምር ነው:: ከሁሉም በፊት ግን ከገደለንና ብዙ ነገር ካሳጣን፣ እያሳጣንም ካለው ብሔር ተኮር እሳቤ መውጣት ግድ ይለናል:: ብሩህ ነጋችን ያለው በትልቁ ተስፋችን ውስጥ ነው:: አሁኑኑ ራሳችንን ከነሙሉ ቀልባችን ልናገኘው ይገባል:: ከነሙሉ ቀልብ መገኘት ራስን በትክክለኛ ቦታ ላይ ትክክል ሆኖ ማግኘት ማለት ነው:: ከነሙሉ ቀልባችን ስንገኝ ትናንሽና ውዳቂ ሀሳቦች አይፈነጩብንም:: ኸረ እንዲያውም አጠገባችንም አይደርሱም:: ትልቁ ተስፋችን በሕይወት ውስጥ የማይጠቅሙንን ሞታዊ መከራችንን የሚዋጋልን ጋሻና ጦራችን ነው:: ከነሙሉ ቀልብ መገኘታችን ይሄን ትልቅ ተስፋችንን ወደ ውጤት ለመቀየር በምናደርገው ትግል ውስጥ ቀዳሚው መስፈርት ነው:: ትልቁን ተስፋ የእኛ ስናደርግ በሕይወታችን ውስጥ፣ በአገራችን ውስጥ የተበላሹ ብዙ ነገሮች መስተካከል ይጀምራሉ:: በተስፋ ወደ ፊት...፤ ለዛሬው አበቃው፤ ሰላም!

> **ትላልቅ ተስፋዎች ትላልቅ ሰዎችን የመፍጠር ኃይል አላቸው፡፡ በትላልቅ ተስፋ የተፈጠሩ ትላልቅ ሰዎች ደግሞ በአካል፣ በአእምሮ፣ በሥነ ልቦናና በኢኮኖሚ አቅማቸው የተገነቡ ናቸው፡፡ እኚህ ግለሰቦች ለአገር የሚሆን ብዙ ነገር ይኖራቸዋል፡፡ እኚህ ግለሰቦች ችግር ፈጣሪ ሳይሆኑ ችግር ፈቺ ናቸው፡፡ በነዚህ ግለሰቦች የተፈጠረች አገር ደግሞ ከፍ ያለ ገጽታ ይኖራታል፡፡ በትልቅ ተስፋ ውስጥ መኖር ራስን በትልቅ አገራዊ እውነት ውስጥ ማስቀመጥ ነው፡፡ አሁን ላይ አገራችን ላለችበት ማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ቀውሶች ችግር ፈጣሪዎች ሳይሆኑ በእውቀትና በተስፋ የተካኑ ችግር ፈቺ ዜጎች ያስፈልጋሉ**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የድሮን ቴክኖሎጂን በራስ አቅም- በደምቢዶሉ ዩኒቨርሲቲ መምህሩ

**ዳግም ከበደ**

የላቀ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ክህሎት ያላቸው ወጣቶች ለአገር እድገት ጉልህ ድርሻ ያበረክታሉ። ብሩህ አእምሮውን ተጠቅሞና እይታዎቹን አስፍቶ አዲስ የቴክኖሎጂ ግኝት የሚፈጥርን ወጣት የሚያበረታታ መንግሥት ደግሞ ከሚጠበቀው ፍጥነት በተሻለ ሁኔታ የሚመራትን አገር ብልፅግና ለማረጋገጥ ዕድሉን ያገኛል። ለዚህም ነው ዓለምን በአዲስ አቅጣጫ እየወሰዳት ያለውን የዲጂታል፣ ቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ውጤት በአግባቡ የሚረዱ፣ የሚግባቡና ከዚያም አለፍ ሲል የራሳቸውን ድርሻ የሚያበረክቱ ወጣቶችን ማፍራት፣ ማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት እንደሚያስፈልግ የዘርፉ ባለሙያዎች የሚናገሩት።


በኢትዮጵያ ላለፉት ዘመናት በሙሉ አቅም በሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ዘርፍ ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ታዳጊዎች የሚያበረታታ ሰፊ ፕሮጀክት አልታየም ነበር። ሆኖም ዓለም የሚመራበት ሥርዓት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መቀየርን ተከትሎ አሁን አሁን መንግሥት የተለየ ትኩረት እንዲሰጥ እያደረገው ይገኛል። ቀደም ካሉት ጊዜያት በተሻለ ሁኔታም ታዳጊና ወጣት የፈጠራ ባለሙያዎች ዘርፉን በመቀላቀል ክህሎታቸውን ለማዳበር ሲተጉ ይስተዋላል። የትምህርት ተቋማትና መሰል ማሰልጠኛዎችም ለቴክኖሎጂና ፈጠራ ሥራዎች የሚሰጡት ትኩረት እየጨመረ መጥቷል። ይህንን ተከትሎ ታዳጊዎችና ወጣቶች ልዩ ተሰጧቸውን ተጠቅመው የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ። ለዚህ በርካታ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል።

የዝግጅት ክፍላችንም ለዛሬ ከፈጠራ ሥራ ጋር በተያያዘ ስኬታማ ውጤቶችን እያስመዘገበ የሚገኝ ወጣት መምህር እንግዳ በማድረግ በዘርፉ ላይ እየታዩ ስላሉ ውጤቶችን ለመቃኘት ወድዷል። በተለይ የፈጠራ ባለሙያው ያስተዋወቃቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ምን ይዘት እንዳላቸው እንመለከታለን።

ወጣቱ አማኑኤል ባልቻ ይባላል። በደንቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል ላብራቶሪ መምህር ነው። በፈጠራ ሥራዎቹና በግል አዲስ ነገር ለማስተዋወቅ በሚያደርገውም ጥረት ይታወቃል። ተወልዶ ያደገው በዚያው ደንቢዶሎ ሲሆን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለውም እዚያው ነው። የከፍተኛ ትምህርቱን ደግሞ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ማጠናቀቅ ችሏል። በቢሾፍቱ የደጀን አቪዬሽን ኢንዱስትሪ ለአራት ዓመታት የሠራ ሲሆን ወደ ትውልድ ቦታው ተመልሶም በዩኒቨርሲቲው በቴክኒካል ረዳት በመምህርነትና በግል የፈጠራ ሥራዎች ላይ ተሰማርቶ ይገኛል።

«ከልጅነቴ ጀምሮ የቴክኖሎጂ ጉዳዮች ላይ ልዩ ፍላጎት ነበረኝ» የሚለው መምህር አማኑኤል፤ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት በቤት ውስጥ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ልዩ ልዩ ነገሮችን ይሠራ እንደነበር ይናገራል። ወደ 10 እና 11ኛ ክፍል በሚገባበት ወቅት ደግሞ በትክክልም ጠቀሜታ የሚሰጡና የተለያዩ የቴክኖሎጂ ሥራዎች ላይ ትኩረት ያደርግ ነበር። ከዚህ ውስጥ የቤት ውስጥ የማብሰያ ቁሳቁሶችን ከአየር ላይ መውረጃና መንሳፈፊያ (የፓራሹት ) እና አነስተኛ አውሮፕላኖችን ለመሥራት ጥረት ያደርግ ነበር። ሥራዎቹን ለትምህርት ቤቱ አቅርቦ በውድድሮች ላይ ለበርካታ ጊዜ አሸንፏል።

በኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ ከዋና ዋና ከተሞች ራቅ ባሉ አካባቢዎች መሰል የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት ብዙ እንቅፋቶች እንዳሉ እሙን ነው። መምህር አማኑኤል የዚህ ፈተና ተጋፋጭ ነበር። ይሁን እንጂ ውስጡ የሚሻውን በቴክኖሎጂ ሥራዎች ብቁ የመሆን ህልም ለማሳካት እነዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አልገደቡትም። ይልቁንም የጥንካሬው ምንጭ ሆነውታል። «በዋና ከተማዎች የፈጠራ ሥራዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ ዕቃዎች ማግኘት በአንፃራዊነት ይቀላል» የሚለው አማኑኤል ይህ አጋጣሚ ባይፈጠርም እንኳን ጠንካራ ፍላጎት በውስጡ ስለነበር ፈተናውን ለማለፍ እንዳልገደበው ያስረዳል። የፈጠራ ባለሙያ በአካባቢ በሚገኝ ቁስ ላይ ተመስርቶ ሃሳቦችን ከግብ ማድረስ እንደሚኖርበትም ተናግሯል።



**የመምህር አማኑኤል ባልቻ የፈጠራ ስራ በሙከራ ላይ**

መምህር አማኑኤል በቢሾፍቱ ደጀን አቪየሽን በሚሠራበት ወቅት አውሮፕላን የመሥራት ህልሙ ከፍተኛ ነበር። በዚያ ሦስት አነስተኛ አውሮፕላኖችን በማሳያነት በመሥራት ዋናውንና ትልቁን አውሮፕላን ለመሥራት ብዙ ጥረት አድርጎ ነበር። የፕሮጀክቱ ንድፍና ፅንሰ ሃሳብም አሁን ድረስ አለው። ለሙከራ የሠራቸው ትናንሽ አውሮፕላኖች ለሦስት ደቂቃ ያህል በአየር ላይ መንሳፈፍ ችለዋል።

«አብዛኛው ተማሪ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሲገባ ወደሚፈልገው ሙያ ውስጥ አይገባም» የሚለው መምህር አማኑኤል እርሱ ግን አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ሲመደብ በአጋጣሚ የሚወደውንና ፍላጎቱ የሆነውን የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት የማጥናት ዕድል እንዳጋጠው ይናገራል። ይህ አጋጣሚም የመፍጠር ፍላጎቱን ይበልጥ እንዳነሳሳውና ብዙ ፕሮጀክቶችን እንዲቀርፅ እንዳስቻለው ያስረዳል። በአርባምንጭ የአራተኛ ዓመት ተማሪ በነበረበት ወቅትም የአርቴፊሻል ኢንተለጀንት የፈጠራ ዘርፍ ላይ በአልሙኒየም ቺፍሜታ ሮቦት መሥራቱን ያስታውሳል።

መምህር አማኑኤል አሁን በደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል በላብራቶሪ ውስጥ መምህር ነው። ተማሪዎቹን በተግባር ውጤታማ የፈጠራ ሥራዎች ላይ በምን መልኩ መሳተፍ እንደሚችሉ ከራሱ ተሞክሮ ያስተምራል። በርካታ የፈጠራ ሃሳቦች ላይ አተኩሮም ችግር ፈቺ ሥራዎች ለመሥራት ፕሮጀክቶችን ይነድፋል። አሁን አንድ ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራ ላይ በዋናነት እየሠራ ነው። በዚህም ሁለት ዓይነት ድሮኖችን በመሥራት እያስተዋወቀ ይገኛል። ለመሆኑ የፈጠራ ባለሙያው የድሮን ሥራ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ለምን አገልግሎትስ ይውላል? ከዚህ የሚከተለው የመምህር አማኑኤል ገለፃ ምላሽ ይሰጠናል።

### የድሮን የፈጠራ ሥራ

ዓለማችን የረቀቁ ቴክኖሎጂ ውጤት ባለቤት እየሆነች ነው። ከዚህ ውስጥ በርካታ አገራት የሚፎካከሩበት ረቂቅ ሳይንሳዊ ፈጠራ ውስጥ ደግሞ ሰው አልባ በራሪ ድሮን ይገኝበታል። ይህ ቴክኖሎጂ መተዋወቅ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አያሌ ለውጦችን ምድራችን አስተናግዳለች። የግብርና፣ ማዕድን፣ የንግድ፣ የፊልም ኢንዱስትሪ እንዲሁም ወታደራዊ ሳይንስ ፈጣን ለውጦችን ማስመዝገብ ችለዋል። የእርስ በእርስ ፉክክሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ለዚህ እንደ ማሳያ የሚሆነው በቱርክ ለወታደራዊ ተልዕኮ የሚመረቱት ድሮኖችን ማንሳት ይቻላል። እነዚህ ድሮኖች በጦርሜዳ ተልዕኮ ውጤት ቀያሪ እየተባሉ ይጠቀሳሉ።

መምህር አማኑኤል ከበርካታ የፈጠራ ሙከራና ተግባሮች በኋላም የፈጠራ ክህሎቱን በልዩ ሁኔታ ሰው አልባ ድሮን መሥራት ላይ እንዲያደርግ በዓለማችን ላይ እየታየ የመጣው ፈጣን የቴክኖሎጂ ለውጥ መነሻ ሆኖታል። በዚህም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሁለት ዓይነት ድሮኖችን መሥራት ችሏል። የመጀመሪያው የድሮን ፈጠራ ሥራው «መልቲኮፕተር» የሚባል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መሬት ላይ ተንደርድሮ የሚነሳ «ፊክስድ ዊንግ ድሮን» የሚባለው ዓይነት ነው። ሁለቱም «አርዶ ኮፍተርና» «ኬኬ ቦርድ» በሚባሉ የበረራ መቆጣጠሪያ የሚሠሩ ናቸው።

መምህር አማኑኤል በመጀመሪያ ድሮን ለመሥራት ሲነሳ አገልግሎቱ እንዲሆን የፈለገው በሚያስተምርበት ደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ለሚገኝ ሰፊ እርሻ ለዘር፣ ፀረ ተባይና መሰል የቅኝት አገልግሎት እንዲጠቅም በማሰብ ነበር። ይሁን እንጂ ይህን ሃሳቡን መሬት ላይ ለማውረድ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ የሠራቸው ድሮኖች ለተለያየ አላማ እንዲውሉ በማድረግ እንዲተገበሩ አድርጓቸዋል። ለምሳሌ በእርሱ የፈጠራ ውጤት የተሠሩት ድሮኖች ዕቃ ለማድረስ፣ ቅኝት ለማድረግና ሌሎች ተግባሮችንም ለማከናወን እንዲችሉ አድርጎ በማንኛውም ጊዜ ማቀናጀት እንደሚቻል ነግሮናል።

መምህር አማኑኤል በማሳያነት የፈጠራቸውን ሁለት ድሮኖች ወደ ተግባራዊ ሥራ ለማስገባትና በስፋት እንዲመረቱ ለማድረግ ጥረት እያደረገ እንደሆነ ይገልፃል። በተለይ የእርሱን ሃሳብ የሚደግፉ አካላት ድሮኖቹን ለማምረት የሚያስችል ወርክ ሾፕ ለመሥራት በሂደት ላይ እንዳሉ ይናገራል። በመጪው ሁለት ወራት ውስጥም ለግብርና ምርት መቀላጠፍ የሚረዱ ድሮኖችን ለመሥራት እያሰበ መሆኑን ይገልፃል። ሁለተኛው እቅዱ ደግሞ በአደጋ ጊዜ እሳት ለማጥፋት የሚያስችሉ ድሮኖችን በተመሳሳይ ማምረት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ረጃጅም የኤሌክትሪክ ምሰሶና ገመዶች ላይ የሚቀመጡ አላስፈላጊ ቁሶችን በእሳት አቅልጦ ማውረድ የሚያስችሉና የኤሌክትሪክ ስርጭት እንዳይስተጓጎል የሚረዱ ተመሳሳይ የድሮን ምርቶችን የማስተዋወቅ እቅድ ነድፎ እየሠራ ነው።

### መምህርነትና የተግባር ምሳሌ

ወጣት አማኑኤል በደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ላብራቶሪ አስተማሪ እንደመሆኑ መጠን ለተማሪዎቹ በሚሠራቸው የፈጠራ ሥራዎች አማካኝነት መነቃቃትን እየፈጠረ ይገኛል። ከዩኒቨርሲቲው ውጪ ባሉ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ታዳጊ ተማሪዎችም በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚዘጋጁ ስልጠናዎች ላይ እየተገኘ ተሞክሮውን ያጋራቸዋል። የፈጠራ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩና «እኔም እችላለሁ» የሚለው መልካም መነቃቃት እንዲሰርፅባቸው የቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል።

### የመምህሩ ራእይ

መምህር አማኑኤል በሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሥራ ላይ እሩቁ የመጓዝና ስኬታማ ሥራዎችን ለአገሩ ለማበርከት ህልም አለው። በተለይ በአቪዬሽን ቴክኖሎጂ ላይ የመሳተፍ ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው። ከልጅነቱ ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ተመርቶ አገልግሎት መስጠት የሚችል የአውሮፕላን አምራች ካምፓኒ የመመስረትና የመፍጠር ራእይ ይዞ በረጅም ጊዜ እቅድ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

የፈጠራ ባለሙያና መምህሩ ሌሎች በርካታ ችሎታዎች አሉት። በአንድ የሙያ ዘርፍ ላይ ብቻ መገደብን አይሻም። ከዩኒቨርሲቲ ውጪ በቤቱ ውስጥ በፈጠራ ላይ የተመረኮዙ የእንጨትና ብረታ ብረት ሥራዎችን ያከናውናል። በተለይ ለግንባታ ግብአት የሚውል ብሎኬትን በቀላሉና ወጪን በሚቆጥብ መንገድ የሚያመርት ማሽን የመሥራት ግብ ሰንቆ ለተግባራዊነቱ እየሠራ ይገኛል። በእንጨት ሥራ ጣውላ መሰንጠቂያና በግብርናው ዘርፍ ደግሞ የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን የመሥራት እቅዶችም አሉት።

መምህሩና የፈጠራ ባለሙያው ከላይ ያነሳቸውን ሃሳቦች እውን ለማድረግ የሚመለከተው የግልም ሆነ የመንግሥት ተቋማት እገዛና ማበረታታትን እንደሚፈልግ በማጠቃለያ ሃሳቡ ላይ ያነሳል። በተለይ ወጣትና ታዳጊ የፈጠራ ባለሙያዎች ወደ ህልማቸው መቅረብ እንዲችሉ አቅም ባላቸው አካላት ሊበረታቱ እንደሚገባም ይገልፃል። እርሱ አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ በርካታ አካላት እንደደገፉት ሳይሸሽግ በተለይ አሁን የሚያስተምርበትን የደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲና በዚያ የሚሠሩ ባልደረቦቹንና የደገፉትን ግለሰቦች ያመሰግናል።

በማጠቃለያ መልዕክቱም «ወጣትና ታዳጊ የፈጠራ ባለሙያዎች ህልማቸውን ከግብ ለማድረስ ትግል ማድረግ ይኖርባቸዋል» በማለት በተለይ በውስጣቸው የተጠነሰሰው ፕሮጀክት መሬት ነክቶ የማህበረሰባቸውን ችግር መቅረፍ እስከሚችል ድረስ ጥረታቸውን ማቆም እንደማይኖርባቸው ይመክራል። እራሱን እንደ ምሳሌ በማንሳትም ለሚሠራቸው የፈጠራ ሥራዎች ተስፋ እያየ የመጣው ከፍተኛ ትግልና ጥረት በማድረጉ መሆኑን አንስቶ በተመሳሳይ ታዳጊና ወጣት የፈጠራ ባለሙያዎችም ህልማቸው ጋር ለመድረስ ተመሳሳይ ነገር ማድረግ እንደሚኖርባቸው በመምከር ሃሳቡን ይቋጫል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የፍራንኮ ቫሉታው ሁለት መልክና ቀጣይ የቤት ሥራዎች

**ታምራት ተስፋዬ**

የገንዘብ ሚኒስቴር እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ማረጋጋት እንዲቻልና መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች የሆኑት ዘይት፣ ስንዴ፣ ስኳር፣ የሕፃናት ወተት እና ሩዝ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፍቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ ኮሚሽን በኩል በቀጥታ እንዲገቡ መወሰኑን ከቀናት በፊት አሳውቋል።

ውሳኔውም በርካታ የውጭ አገር የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት የራሳቸውን ሚና መጫወት እንዲችሉ የፍራንኮ ቫሉታ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን ተከለትሎ የተላለፈ መሆኑንም ሚኒስቴሩ ገልጿል።

ቀረጥና ታክስን በሚመለከት በገንዘብ ሚኒስቴር በ22/3/2013 ዓ.ም በቁጥር ማአ.30/7/51 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት እንዲፈጸም፤ አፈጻጸሙን በተመለከተ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበትም አሳውቋል።

ፍራንኮ ቫሉታ ሕጋዊ ከሆነ ምንጭ የሚገኝ የውጭ ምንዛሪ ማለት ሲሆን፣ ይህም የባንክ ቤት ፈቃድ ሳያስፈልግ የሚገቡ ምርቶችን ወደ አገር ለማስገባት የሚያስችል የፈቃድ ዓይነት ማለት ነው። መብት ያላቸው አስመጪዎች ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገቧቸው ምርቶች የውጭ ምንዛሬን በተመለከተ በብሔራዊ ባንክ የወጡ እና በንግድ ባንኮች የሚተገበሩ ጥብቅ መመሪያዎችን የማለፍ ግዴታ የለባቸውም።

ውሳኔው በተለይ ከ35 በመቶ በላይ ሆኗል የሚባለውን የዋጋ ግሽበት ለማረጋጋት ምን አበርክቶ ይኖረዋል፣ ከውሳኔ ጋር ተያይዞስ ምን ስጋቶች ይኖራሉ፣ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎችስ ምን ሊሆኑ ይገባል በሚል ጥያቄዎችን በማንሳት አዲስ ዘመን ጋዜጣም የተለያዩ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎችን አነጋግረናል።

አስተያየታቸው ያጋሩን የምጣኔ ሀብት ምሁራንም፣ መንግሥት በከፍተኛ ወጪ በመግዛት በዝቅተኛ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ከሚያቀርባቸው መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች በተጨማሪ በሌሎች አካላት የሚገባውን በማከል አቅርቦቱ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምር ዘንድ ያለውጭ ምንዛሪ ሸቀጦችን የማስገባት አሠራር መፈቀዱ፣ እየታየ ላለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ጊዜያዊ ማስተንፈሻ ጥሩ የመፍትሔ አማራጭ እንደሆነ ይስማሙበታል። ይሁንና ደግሞ የፍራንኮ ቫሉታው ትግበራው በሚፈለገው መንገድ መራመድ ካልቻለ አደጋው ከባድና እጅግ የከፋ ስለመሆኑም ያስገነዝባሉ።

በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸው ከጠየቅናቸው መካከል አንዱ የሆኑት በሃረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር ዶክተር ሞላ አለማየሁም፣ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ምርቶችን ማስገባት በተለይ የገቢ ንግድን ለማሻሻል እና ለማረጋጋት በተለያዩ ጊዜያት ሲፈቀድ ተመልሶም ሲከለከል ሲነሳ መቆየቱ ያስታውሳሉ።

ፍራንኮ ቫሉታ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በተለይ የአገር ኢኮኖሚ ሲንገጫገጭና ግሽበት ሲከሰት ዋጋን ከማረጋጋት አንፃር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለውም የሚያመላክቱት ዶክተር ሞላ፣ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ተግባራዊ መደረጉም በተለይ የዋጋ ንረትን በማረጋጋት ረገድ ዓይነተኛ ሚና እንደሚጫወት ያሰምሩበታል። ‹‹መንግሥት ይህን ውሳኔ ያሳለፈው አቅርቦትና ፍላጎቱ መመጣጠን ባለመቻሉ እና የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማረጋጋት ነው›› ይላሉ፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዘመዴነህ



ዶክተር ሞላ አለማየሁ

ንጋቱም፣ መንግሥት ፍራንኮ ቫሉታን መፍቀዱ የዋጋ ግሽበቱን ለመቀነስና የምርት አቅርቦትን ለመጨመር እንደሚረዳ ይገልፃሉ። የአገር ውስጥ ፍላጎትና አቅርቦትም አለመመ ጣጠንን በማስተካከል፤ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትና የምርት እጥረትን ለመቅረፍ ጥሩ መፍትሄ ተደርጎ እንደሚታይም ይጠቁማሉ።

የውጭ ምንዛሬ ከዋነኞቹ የዋጋ ንረት ምክንያቶች የሚመደብ መሆኑን የሚያስረዱት ሌሎች የምጣኔ ሀብት ምሁራንም፣ አነስተኛ የውጭ ምንዛሬ ክምችት ባለበት ጊዜ የውጭ አገራት ገንዘብ ሁሉ የግድ ከባንክ መወሰድ አለበት ብሎ ሙጥኝ ማለት ትክክል እንዳልሆነና የፍራንኮ ቫሉታ አማራጭም የግድ እንደሆነም ያሰምሩበታል።


‹‹ይሁንና የፍራኮ ቫሉታው ትግበራ ሌላ ችግር እንዳያመጣ መጠንቀቅ የግድ ነው›› ይላሉ። የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ክቡር ገናም ይህን እሳቤ ይጋሩታል። ፍራንኮ ቫሉታ ያላግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል መጠንቀቅ እንደሚገባ አጽእኖት የሚሠጡት አቶ ክቡር፣ የፈቃዱን ዓላማ ለማሳካት ሳይሆን የራሳቸውን ጥቅም ለማዳበር የሚፈልጉ ግለሰቦች ያላግባብ እንዳይጠቀሙበት ሂደቱ በጥብቅ ሥነ ምግባር እንዲመራ ማድረግ እንደሚገባም ያሰምሩበታል።

ዶክተር ሞላ አለማየሁም ቢሆን ‹‹ፍራንኮ ቫሎታ አመራጭ መፍትሄ ከመሆኑ ባሻገር የራሱ የሆኑ ፈተናዎችን ይዞ የሚመጣ ነው›› ይላሉ። የመንግሥትን ፖሊሲ በአግባቡ እንዳይሳለጥ የማድረግ አቅም እንዳለው በመጠቆም፣ በርካታ አገራት አማራጩን ተግባራዊ ከማድረግ የሚቆጠቡትም በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች መሆኑንም ያስገነዝባሉ።

እንደ ዶክተር ሞላ ገለጻም፣ በፍራንኮ ቫሉታ ትግበራ ወቅት ከቁጥጥር ጋር በተያያዘ በሚስተዋሉ ድክመቶችና በሚፈፀሙ ሕገ ወጥ ተግባራት አገር የሚያስፈልጋትና ወደ አገር የሚገባው የተለያየ ሊሆንም ይችላል። ተጠቃሚዎቹ እንጂ አገር የምትፈልገው ላይገባ የሚችልበት ዕድልም ሰፊ ነው።

ተጠቃሚዎቹ ትርፍን ብቻ ታሳቢ በማድረግ የሚፈልጉትን ምርት ወደ አገር ውስጥ አስገቡ ማለት ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአገርን ኢኮኖሚ ይጎዳል። ገበያ ላይ ያሉ በተለይ በአገር ውስጥ መመረት የሚችሉት ሳይቀር በዝቅተኛ ዋጋ የሚገቡ ከሆነ ደግሞ የአገር ውስጥ አምራቾችን ያደቃል። በማደግ ላይ ያሉ ፋብሪካዎችን ያቀጭጫል።

በጉዳዩ ላይ የተለያየ ምልከታቸው የሚያጋሩ ዓለምአቀፍ የምጣኔ ሀብት ምሁራንም፣ ፍራንኮ ቫሉታ፣ በተለይ የጥቁር ገበያን በማስፋፋት ረገድ ከባድ ተፅእኖ እንዳለው በመጠቆም፣ ችግሩ እንዳይከሰት አስቀድሞ መከላከል የሚቻልበትን መንገድ መቀየስ ካልተቻለም አደጋው ከባድ



አቶ ክቡር ገና

ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ።

‹‹ከሁሉ በላይ በወንጀል የተገኘ ገንዘብንም በእግረ መንገድ ሕጋዊ ለማድረግ ዕድል ይሰጣል›› የሚሉት የምጣኔ ሀብት ምሁራኑ፣ አሠራሩ ጥንቃቄ ካልተደረገበት ግለሰቦች በትይዩ ገበያ ገዝተው ያስቀመጡትን ወይም ያጠራቀሙትን የውጭ ምንዛሪ የሚያጥቡበት ወይም ሕጋዊ የሚያደርጉበት ሁኔታን ሊያመቻች እንደሚችል ይጠቁማሉ።

በተለይ የትግበራው ዕድል ተጠቃሚ ግለሰቦች አጋጣሚውን በመጠቀም ከጥቁር ገበያ ዶላር እየገዙ የተፈቀዱትን ዕቃዎች በፍራንኮ ቫሉታ ስም በማስገባት እንደገና የጥቁር ገበያው ጡንቻ እንዲፈረጥም ያደርጋል የሚል ስጋታቸውንም ያስቀምጣሉ።

ዶክተር ሞላ አለማየሁም፣ ውሳኔውን ተከትሎ የጥቁር ገበያ ጉዳይ ዋነኛው አደጋ ስለመሆኑም ያሰምሩበታል። ውሳኔው ለጥቁር ገበያው (Black Market) መስፋፋት በተለይም ሕጋዊ ያልሆነን ገንዘብ ሕጋዊ የማድረጊያ አንዱ መንገድ ሊሆን እንደሚችል በመጠቆም፣ ይህ እንዳይሆን በማድረግ ረገድም መንግሥትን ከባድ ቤት ሥራ እንዳለበት ያስገነዝባሉ። በፍራንኮ ቫሉታው ትግበራ ከሁሉ በላይ ጠንካራ ቁጥጥር እጅግ ወሳኝ ስለመሆኑም አፅእኖት ይሰጡታል።

የፍራንኮ ቫሉታ መብት መፈቀድ ጥቁር ገበያን ለመቆጣጠር ሲባል በውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም ላይ የወጡ የተሻሻሉ መመሪያዎችን የሚፃረር እንደሆነም የሚከራከሩ ባለሙያዎች አሉ። የተሻሻሉት መመሪያዎች ዋነኛ ግብ በጥቁር ገበያ የሚፈጸመውን ሕገወጥ ድርጊት ለመከላከል ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ፍራንኮ ቫሉታ ተፈቀደ ማለት ጥቁር ገበያን መደገፍ ሊሆን እንደሚችል ሌላው የኢኮኖሚ ባለሙያዎች የሚያቀርቡት አስተያየት ነው።

በፍራንኮ ቫሎታው ተጠቃሚ የሚሆኑ ግለሰቦች የውጭ ምንዛሪ ምንጭን ማሳወቅ እንደ ግዴታ መቀመጡ ተገቢ ቢሆንም፤ ብሔራዊ ባንክ ምንጩን የማረጋገጥ ግዴታ ተከታትሎ የማስፈጸም አቅሙ ደካማ ከሆነ መመሪያው አደገኛ መሣሪያ የመሆን ዕድል እንደሚኖረው የሚገልፁም በርካቶች ናቸው።

በፍራንኮ ቫሉታ ለሚገባው ዕቃ አስመጪው የሚያቀርበውን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ብሔራዊ ባንክ እንደሚያረጋግጥ ቢታመንም፣ ብሔራዊ ባንክ የገንዘቡን ምንጭ እንዴት ያረጋግጣል? ለሚለው ጥያቄ እስካሁን የተሰጠ ማብራሪያ የለም።

ዶክተር ሞላ አለማየሁ፣ ለበጎ የታሰበው በፍራንኮ ቫሉታ ሸቀጦችን ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ውሳኔ ሌላ ችግር እንዳያመጣ መሠራት ስላለበትም የቤት ሥራ ሲጠቁሙም ከሁሉ በላይ ውጤቱን መገምገም የግድ እንደሆነም ያሰምሩበታል። ‹‹መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ያለ ውጭ ምንዛሪ ፈቃድ በቀጥታ እየተፈቀደ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ በመወሰኑ ውጤቱ ታይቷል፤ ገበያውስ ተረጋግቷል ወይ የሚለው መሠረታዊ ጉዳይ በየጊዜው መቃኘት ያስፈልጋል›› ይላሉ።

‹‹አፈፃፀሙን በየጊዜው መከታተል የግድ ይላል። የተፈለገውን ውጤቱን አምጥቷል አላመጣም፣ የሚለውም መገምገም አለበት። ከዚህም ከፍ ሲል ውጤቱ እየታየ ማሻሻያዎች ካስፈለጉም ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላልም›› ነው ያሉት።

ችግሩ የአገሪቱን የፋይናንስ ሥርዓት ብሎም ግብይት ሊያናጋው ስለሚችል ከሁሉ በላይ በትግበራው ሂደት ጠንካራ ቁጥጥር እጅግ ወሳኝ ስለመሆኑም አፅእኖት የሚሠጡት ዶክተር ሞላ አለማየሁ፣ ለዚህ ደግሞ የተለየ ስልት መንደፍ እንደሚገባና ብሔራዊ ባንክም ሆነ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ነው ያስገነዘቡት።

ከዚህ ባሻገር ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት ምርቶች መንግሥት ፈቃድ የሰጣቸው ናቸው አይደሉም የሚለውን ይበልጥ መከታተል እንደሚያስፈልግም አፅእኖት የሚሠጡት ዶክተር ሞላ፣ ይህን ኃላፊነትም የጉምሩክ ኮሚሽንም ብሎም የንግድ ሚኒስቴር በከፍተኛ ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸውም ነው ያሳሰቡት።

ከተዓማኒነት አንፃር የፍራንኮ ቫሉታ ዕድል እንዲጠቀሙ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት መረጃ ሊቀርብ ይገባል እና ፍራንኮ ቫሉታ አስታከው ሌሎች ግብዓቶች ማምጣት አለማምጣታቸው መፈተሽ ያስፈልጋል በሚለው ይስማሙበታል።

የፍራንኮ ቫሉታው ውሳኔ በተለይ የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት የአጭር ጊዜ እንጂ ዘላቂ መፍትሄ እንዳልሆነ የሚያስገነዝቡት የምጣኔ ሀብት ምሁራኑ፣ ይህ እንደመሆኑም ችግሩን ለመሻገር ተጨማሪ መፍትሔዎች ማስተዋወቅ የግድ እንደሚልም ያስገነዝባሉ።

የፍራንኮ ቫሉታ ተግባራዊነት አሁንም የዋጋ ንረቱን ሊያረጋጋው ወይም ላያረጋጋው እንደሚችል የሚያመላካቱት አቶ ክቡር ገና፣ ፍራንኮ ቫሉታ በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ችግር እንዲፈታ እንጂ፤ ለረጅም ጊዜ የሚሆን መፍትሄ እንዳልሆነም ይገልጻሉ።

በተለይም ከሰላምና ጸጥታ ጋር ተያይዞ የሚነሱት ችግሮች ፈጣን እልባት መስጠት እንዲሁም፣ አስፈላጊ ምርቶችን ለማምረት የሚጠቅሙ መሆኑን የገለጹት አቶ ክቡር፣ ከፖሊሲ ጀምሮ የምርት አቀራረብና የምርት እድገት፣ የምርት ጥራት፣ የገበያ አቅርቦት፣ ሎጂስቲክስና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግም ነው ያብራሩት።

ፍራንኮ ቫሉታ ጊዜያዊና የአጭር ጊዜና ምላሽ መስጫ መፍትሄ ስለመሆኑ የሚስማሙበት አቶ ዘመዴነህ ንጋቱም፣ ለመፍትሔውም በቋሚነት የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ እና ከውስጥ ፍላጎት አልፎም የውጭ ምንዛሬ ማስገባት የሚያስችሉ ዋና ዋና ምርቶችን በስፋት ማምረት ብሎም ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንደሚጠቅም አመልክተዋል።

‹‹ፍራንኮ ቫሉታ ጊዜያዊና ችግሮቹ ይበልጥ እንዳይባባሱ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ለአጭር ጊዜ የሚሆን ማስተንፈሻ ነው።በተለይ ከዕለት ዕለት እየተባባሰ የመጣውን ዋጋ ግሽበት ፈር ለማስያዝ ዘላቂው መፍትሄ የአገሪቱን መዋቅራዊ ኢኮኖሚ ሒደት ማስተካከል ይገባል»የሚሉት ዶክተር ሞላ አለማየሁ በበኩላቸው፣ በተለይ ፍላጎትና አቅርቦት ምጥጥን ልዩነቱን ለማስተካከል አገር ውስጥ በተሻለ ማምረት የሚችልበትን መንገድ መቀየስና ለዚህ ተግባራዊነትም ሌት ተቀን መትጋት እንደሚያስፈልግ አፅእኖት ሰጥተውታል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የትብብር ስምምነት ለሴቶች ተጠቃሚነት

**አስናቀ ፀጋዬ**

ሴቶች የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ናቸው እየተባለ በተደጋጋሚ ሲነገር ይደመጣል። በተወራው ልክ ግን ሴቶች ለበርካታ አመታት በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ ሲሆኑ አልታየም። በተለይ ደግሞ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያን ያህል አልነበረም።

በጊዜ ሂደት የሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም ብዙ እንደሚቀረው ብዙዎችን ያስማማል። በርግጥ ሴቶች ተቀጥሮ ከመሥራት ጀምሮ በአነስተኛና ጥቃቅን ተደራጅተው እንዲሠሩ በመንግሥት በኩል በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ወደ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተሸጋግረው እንዲሠሩም ድጋፍ ሲደረግላቸው ቆይቷል።

ሆኖም በእነዚህ ዘርፎች ሴቶችን በኢኮኖሚ ለማብቃት በመንግሥት በኩል ሲደረግ የነበረው ጥረት አርኪ ሆኖ አልተገኘም። በተለይ ደግሞ ለሴቶች የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ አሁንም ክፍተቶች እንዳሉ ይስተዋላል። ከዚህ አንፃር የግሉ ዘርፍ ሚና የጎላ ቢሆንም ከሚሸከመው የሥራ ዕድል ጋር ሲነፃፀር ብዙ አልተሠራበትም።

የግሉ ዘርፍ ግዙፍ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነውና የሚጠበቅበትን ያህል ከሠራ፤ በተለይ ደግሞ በትብብርና አጋርነት የመሥራትን ሂደት ከተላመደ ለበርካቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ይችላል። በዚሁ የሥራ ዕድል ፈጠራ ታዲያ ሴቶችም ተጠቃሚ ይሆናሉ። በትብብር ለመሥራት ዝግጁ መሆን በተለይ ሴቶችን እንዴት በሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ከሰሞኑ በሁለት የግል ተቋማት መካከል የተደረገው ስምምነት ጥሩ ማሳያ ነው።

‹‹እናት ባንክ›› በኢትዮጵያ በአስራ አንድ ባለ ራዕይ ሴቶች ሃሳብ አመንጪነት የተቋቋመ የመጀመሪያው የሴቶች ባንክ ሲሆን ላለፉት ዘጠኝ አመታት የተሟላ የባንክ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የባንክ አገልግሎት ከመስጠት በዘለለ በተለይ ሴቶችን በኢኮኖሚ የማብቃት ተልዕኮ ይዞ በመንቀሳቀስም ይታወቃል።

ባንኩ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማሳካት የሴቶች ባንክ አገልግሎት መምሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ሴት ሥራ ፈጣሪዎች ብድር የሚያገኙበትን አሠራርም አመቻችቷል። በተለያዩ ዘርፎችና ጊዜያት እናቶችና እህቶች ላበረከቱት አስተዋፅኦ እውቅና ለመስጠትና ለተተኪው ትውልድ አርአያ እንዲሆኑ በማሰብም በአዲስ አበባ የሚከፍታቸው ቅርንጫፎች በእነዚሁ ሴት የአገር ባለውለታዎች ስም እንዲሰየም አድርጓል።

ከዚህም ባሻገር በተለያየ መልኩ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች የማቆያና ድጋፍ ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ትብብር በመፍጠር በባንኩ ውስጥ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣም ይገኛል። በየአመቱ ከሚያገኘው ትርፍ 5 ከመቶ ያህሉን ሥራ መፍጠር ለሚችሉ፤ ነገር ግን ማስያዢያ ማቅረብ ለማይችሉ ይህ ትርፍ እንደማስያዣ እንዲውል በማድረግ ብድር በማበደር በርካታ ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑም አስችሏል።

የሁሉንም ኅብረተሰብ ክፍሎች ፍላጎት በሚያሟላና የሴቶችን የፋይናንስ አካታችነት በሚያጎለብት መልኩ የተለያዩ አሠራሮችን በመከተል የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎቶችን ጨምሮ ሌሎች ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎቶችን እየሰጠም ነው።

የሚሰጠውን አገልግሎት ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በማድረግ ረገድ የቅርንጫፎቹን ቁጥር ከማብዛት ጎን ለጎን የቴክኖሎጂ መሠረትና ሰፊ ተደራሽነት ካላቸው ተቋማት ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል። ባንኩ ከሃይብሪድ ዲዛይን -ራይድ ጋር በስትራቴጂያዊ አጋርነት በትብብር አብሮ ለመስራት ከሰሞኑ ያደረገው ስምምነትም የዚሁ ትብብር አንዱ ማሳያ ነው።

በተመሳሳይ ሃይብሪድ ዲዛይን-ራይድም በሴት የተመሠረተና በቴክኖሎጂ የታገዘ አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎት እያቀረበ ያለ ተቋም ሲሆን የጥሪ ማዕከልን ጨምሮ ለአጠቃቀም አመቺ የሆኑ መተግበሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ ማህበረሰቡ ፈጣን፣ ደህንቱ የተጠበቀና አስደሳች የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ እያደረገ ይገኛል።

በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው ስትራቴጂያዊ አጋርነት ዋነኛ አላማም የእናት ባንክ ዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ከሃይብሪድ ዲዛይን ቴክኖሎጂና ቴክኒካዊ



አቶ ኤርሚያስ እንዳርጌ



ወይዘሮ ሳምራዊት ፍቅሩ

ትብብር ጋር ጥምረት በመፍጠር ጥራት ያለው የባንክና የፋይናንስ ምክር ለማቅረብ፣ ለራይድ ትራንስፖርት አቅራቢ አሽከርካሪዎች የብድር አገልግሎት ለመስጠት፣ ተሳፋሪዎች በባንኩ ሞባይል ባንኪንግ ተጠቅመው ክፍያ እንዲከፍሉ እንዲሁም የራይድ አሽከርካሪዎች ለሃይብሪድ ዲዛይን የሚከፍሉትን ኮሚሽን /ክሬዲት/ ክፍያ በባንኩ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት እንዲከፍሉ ለማድረግ ነው።

ከእነዚህ አላማዎች በዘለለ ታዲያ በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው በትብብር አብሮ የመስራት ስምምነት ለሴቶች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ እሴት የጨመረ እንደሆነም ተነግሮለታል።

አቶ ኤርሚያስ አንዳርጌ የእናት ባንክ ፕሬዚዳንት ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት በእናት ባንክና በሃይብሪድ ዲዛይን ራይድ መካከል የተደረገው አብሮ የመሥራት ስምምነት በሥራ ዕድል ፈጠራ ለሴቶች የተለየ ዕድል ይዞ መጥቷል። ባንኩ ከራይድ ጋር ሲሠራ ሴቶች ሆነው በአሽከርካሪነት የሚሠሩና የተሽከርካሪ ባለንብረቶች በመኖራቸው የዚሁ ስምምነት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ባንኩ በዚሁ ስምምነት መሠረት በዋናነት ለመሥራት ያቀደው ወደእዚሁ የራይድ ቢዝነስ መግባት የሚፈልጉ ሴቶች ካሉ ቁጠባ በማስተማር ገንዘብ በባንኩ ቆጥበው ወደ ሥራ ገብተው ገቢ እንዲያገኙ ነው። ይሄ እንደመንደረደሪያ ቢቆጠርም ባንኩ በቀጣይ ሌሎች ብዛት ያላቸው የሥራ ዕድሎችን ለሴቶች ለመፍጠር የሚሠራቸው ሥራዎች ይኖራሉ። በቀጣይም ባንኩ ከራይድ ጋር የሚሠራቸው ሌሎች ሥራዎች አሉ። እነዚህም ሥራዎች ትኩረታቸው በሴቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ነው። ባንኩ የተቋቋመበት ዋነኛ አላማም ሴቶችን የማገዝና የማብቃት ሥራን መሥራት ነው። ይህንንም ባንኩ በአግባቡ ለመሥራት ቁርጠኛ ነው። ሆኖም ባንኩ ለሁሉም ዕድል የሚሰጥ ባንክ በመሆኑ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የባንኩ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

እናት ባንክ ሴቶች በአብዛኛው በኢኮኖሚ የተጎዱ መሆናቸውን ስለሚያምን ሴቶችን በኢኮኖሚ ቢያበቃ በርካቶችን መጥቀም ይችላል። አንድ እናት ሥራ አገኘች ማለት ደግሞ ቤተሰቧን ደጎመች ማለት ነው። ልጆቿም አይራቡም።

ባንኩ በቀጣይ በሴቶች ላይ ተመሳሳይ ሥራዎችን ለመሥራት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በተለይ ደግሞ ባንኩ ሴቶችን በፋይናንስ ተጠቃሚ የሚያደርግ ክፍል አደራጅቷል። የዚህ ክፍል ዋና ሥራው ለሴቶች እንዴት የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚቻል የሚያጠና ክፍል ነው።

ይህን ስምምነት መነሻ በማድረግም ከዚህ በኋላ ባንኩ ለሴቶች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርና ሴቶች ሥራ አገኝተው ሕይወታቸውን እንዲያሻሻሉ በርካታ ሥራዎች ይሠራል ተብሎ ይጠበቃል።

የሃይብሪድ ዲዛይን-ራይድ መስራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሳምራዊት ፍቅሩ በበኩላቸው እንደሚሉት ራይድና እናት ባንክ ባደረጉት በጋራ የመስራት ስምምነት መሠረት ራይድን መቀላቀል ለሚፈልጉ አዳዲስ ሴት አሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪ ባለንብረቶች እንዲሁም ለወንዶችም ጭምር የሥራ ዕድል ለመፍጠር ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

የራይድ አገልግሎት ፈጣን ገንዘብ የሚገኝበት ከመሆኑ አኳያም በተለይ ራእይ ላላቸው ሴቶችና ወጣቶች ገንዘባቸውን በሌሎች ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች ላይ ለማዋል ያግዛቸዋል። ከዚህ አኳያ አዳዲስ ለሚገቡ ሴቶችና ወጣቶች ሃይብሪድ ዲዛይን-ራይድ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ይገኛል።

በዋናነት ደግሞ ከእናት ባንክ ጋር የተደረገው ስምምነት ሴት አሽከርካሪዎች ከባንኩ ብድር ሲወስዱ በአነስተኛ ወለድ ብድራቸውን እንዲከፍሉ ያስችላቸዋል። ወደ ባንኩ ሲመጡና የራይድ ኮሚሽን /ክሬዲት/ ክፍያ ሲፈፅሙም የተወሰነ ቅናሽ ያገኛሉ። በተለይ ደግሞ የሌላ ሰው ተሽከርካሪ ይዘው የራይድ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ሴቶች የራሳቸው ተሽከርካሪ እንዲኖራቸው ሁኔታዎች ተመቻችቶላቸዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ገለፃ ሃይብሪድ ዲዛይን-ራይድ ራዕዩን ለብዙ ባንኮች የተናገረ ቢሆንም እናት ባንክ ያለምንም ማንገራገር ራዕዩን ተቀብሎ ስምምነት ፈፅሟል። ባንኩ ይህን ራዕይ ተቀብሎ አብሮ ለመስራት የተስማማውም ራይድ እየሠራ ያለውን ሥራ በማየትና የወደፊቱንም እድገት በመመልከት ነው። በምላሹ ሃይብሪድ ዲዛይን- ራይድ እናት ባንክ በተለይ ሴቶች በኢኮኖሚ ብቁ እንዲሆኑ ስለሚያበረታታ በጋራ ለመሥራት ተስማምቷል።

በዚሁ ስምምነት መሠረት ‹‹በእናት ራእይ›› የእናት ባንክ የቁጠባ ፕሮግራም አሽከርካሪዎች ለአንድ ዓመት በመቆጠብ ባንኩ በሚያመቻችላቸው ብድር ተሽከርካሪዎቻቸውን መቀየር ይችላሉ።

‹‹እናት እፎይታ›› በተሰኘው የባንኩ የቁጠባ ፕሮግራምም አሽከርካሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ገንዘብ ሲያጥራቸው ባንኩ የብድር አገልግሎት አመቻችቶላቸዋል። ‹‹በእናት ደራሽ›› ፕሮግራም ደግሞ አዳዲስ አሽከርካሪዎች ወደ ራይድ ገብተው ሥራ የሚጀምሩበትን ብድር ያመቻቻል።

በቀጣይም ሃይብሪድ ዲዛይን-ራይድ በተለይ በሴቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ዙሪያ በርካታ ሥራዎችን ለመሥራት እቅድ ይዟል። አሽከርካሪዎችን በስልክ የማናገር ሥራዎች እየተሠሩም ይገኛሉ። ይህም ሴቶችን ብቻ ሳይሆን ወንዶችንም ጭምር ያካትታል።

**‹‹እናት ባንክ›› በኢትዮጵያ በአስራ አንድ ባለ ራዕይ ሴቶች ሃሳብ አመንጪነት የተቋቋመ የመጀመሪያው የሴቶች ባንክ ሲሆን ላለፉት ዘጠኝ አመታት የተሟላ የባንክ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የባንክ አገልግሎት ከመስጠት በዘለለ በተለይ ሴቶችን በኢኮኖሚ የማብቃት ተልዕኮ ይዞ በመንቀሳቀስም ይታወቃል።**

ራይድ ለሴቶች ትኩረት አድርጎ እየሠራ ያለ ቢሆንም በዋናነት የሚያየው ግን የፆታውን ጉዳይ ሳይሆን የወጣት ሴቶችንም ሆነ ወንዶችን ራዕይ ነው። ራዕያቸውን ለማሳካትና መድረስ የሚፈልጉበት ቦታ እንዲደርሱም ይደግፋል። ከዚህ አንፃር ራይድ የሴትና ወንድ ወጣቶች የራእያቸው ጉዞ አጋር ነው።

በእናት ባንክና በሃይብሪድ ዲዛይን-ራይድ መካከል አብሮ ለመሥራት የተደረገው ስምምነት ተግባራዊ መሆን ሲጀምር ለራይድ አሽከርካሪዎች፣ ለሃይብሪድ ዲዛይን፣ ለባንኩ ብሎም ለሰፊው ማህበረሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት ጥራት ከመጨመር፣ የአከፋፈል ሥርዓትን ከማዘመንና የጋራ ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንፃር የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሚሆን በብዙዎች ዘንድ ተነግሮለታል።

ከዚህ ባለፈ ስምምነቱ ሌሎች የግል ተቋማት በጋራ አብረው ለመሥራት የሚያነሳሳና ሴቶችን ጨምሮ በርካታ ዜጎችን በሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሚያድረጉ ሥራዎችን በጋራ ለማከናወን የሚንቀሳቀስ እንደሆነም ተጠቁሟል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**በዛሬው አዲስ ዘመን ዱሮ አምዳችን ጋዜጣው በ1960ዎቹ ከቀረቡ ዘገባዎች ጥቂቶቹን ይዞ ቀርቧል፡፡ በጋዜጣው ከተዘገቡ ሥራዎች መካከልም የኑሮ ውድነትን የተመለከው ይገኝበታል፡፡ የኑሮ ውድነትን የዚያን ዘመንም ፈተና እንደነበር ከዘገባው እንረዳለን፡፡ ችግሩን ለመፍታት የአዲስ ከተማ አስተዳደር በወቅቱ ያደርግ የነበረውን በጽሑፉ እንቃኛለን፡፡ ዛሬም በትኩረት የሚከናወኑ የኮንትሮባንድ እርድን ለመቆጣጠር ይወሰድ ስለነበረው እርምጃ እና በዘይት ፋብሪካ ልማት ይሠሩ ከነበሩ ተግባሮች መካከል ፋብሪካ መገንባት አንዱ መሆኑን የሚያመለክቱ ዘገባዎችንም ይዘናል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

ኃይለማርያም ወንድሙ

### የአዲስ አበባ ከተማ መማክርት ውይይት አደረጉ

አዲስ አበባ (ኢ-ዜ-አ)፡- የአዲስ አበባ ከተማ መማክርት ትናንት በክቡር ዶ/ር ኃይለጊዮርጊስ ወርቅነህ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሊቀመንበርነት ስብሰባ አድርገው በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ።

መማክርቱ ከተወያዩባቸውም ልዩ ልዩ ጉዳዮች ውስጥ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የደረሰው የእህል ዋጋ መወደድ ሁኔታ ይገኝበታል። ይህንኑ አሳብ ለምክር ቤቱ ያቀረቡትና የገለጡት በምክር ቤቱ የገፈርሣ ወረዳ ግዛት ሕዝብ አማካሪ የሆኑት የተከበሩ አቶ ጌታሁን ሞገሴ ሲሆኑ በዚሁ ጉዳይ ላይ መማክርቱ የአሳብ መለዋወጥ ባደረጉ ጊዜ የከተማው ሕዝብ በልዩ ልዩ መንገድ በተፈጠረው የኑሮ ውድነት ምክንያት የደረሰበትን ችግር በመዘርዘር ሰፋ ያለ አስተያየት ሰጥተዋል ሲል የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የሕዝብ ግንኙነት ማስፋፊያና ማስተዋወቂያ ክፍል በሰጠው ዜና ላይ ገልጧል።

የማስታወቂያ ክፍሉ እንደገለጠው፤ መማክርቱ በተለይ የእህል ዋጋ ይህን ያህል በሚያድግበት ጊዜ የእህል ቦርድ የገበያውን ሚዛን መጠበቅ ይገባዋል፤ የሚል አስተያየት ሠንዝረዋል። እንደዚሁም በፋሲካ በዓል ሰሞን ይህን ያህል እህል ዋጋ ውድ መሆንና ከሚገባው በላይ ወጥቶ መገኘት ያስገረማቸው መሆኑን ገልጠዋል። ከዚህም በቀር ገበያው መልክ ሲያጣ የዋጋ ቁጥጥር መደረግ ይገባዋል በማለት ሠፊ አስተያየት ሰንዝረዋል።

ከዚህም ሌላ እህል ጠፍቶ ነው ወይስ ነጋዴዎቹ ዘግተውበት ነው ? የሚል ጥያቄ አዘል አሳብ ቀርቦ መማክርቱ ሰፊ ውይይት ያደረጉበት መሆኑንና በመጨረሻውም፤ ክቡር ከንቲባው ጉዳዩ ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን ከገለጡ በኋላ፤ ይህንን ጉዳይ በሠፊው ለመረዳት እንዲቻል የንግድ ሚኒስቴር፤ የእህል ቦርድና የነጋዴዎች ወኪሎች ባሉበት ብንወያይበት ይሻላል በማለት ያቀረቡትን አሳብ መማክርቱ በአንድ ዓይነት ድምጽ የተቀበሉት መሆናቸውን የማስታወቂያ ክፍሉ አረጋግጧል።

**ሚያዝያ 13 ቀን 1963 ሰ.ም**

### 5000 ኪሎ ስጋ ተቃጠለ

በአዲስ አበባ ከተማ በተለይም በምእራብ ማዘጋጃ ቤት ክልል ውስጥ ያለ ፈቃድ ሳይመረመሩ የታረዱ ከብቶች 5 ሺ ኪሎ ስጋ ተቃጠለ።

ያለፈቃድ ንጽህናቸው ባልተጠበቀ ስፍራዎች ከብቶች አርደው ሲሸጡ ከተገኙት መካከል አብዛኞቹ ፍርድ ቤት እየቀረቡ ሲቀጡ፣ ሌሎቹም ያራዷቸው ከብቶች ስጋ ተይዞ መቃጠሉን ከምእራብ ጤና ጥበቃ መስሪያ ቤት ተገለጠ።

ከብቶቹ ያለፈቃድ ከቄራ ወጥተው በብዛት የታረዱባቸው ስፍራዎች በአዲሱ ሰፈር አካባቢ፣ በደጃዝማች ገነሜ ሰፈር፣ በኮልፌ፣ በአዲሱ ፯ኛ ወረዳ ፍርድ ቤት አጠገብ፣ ቃጫ ፋብሪካ፣ አለም ጤና ከተባለው መሆኑ በዜናው ተገልጧል።

በአዲሱ ከተማ አካባቢ አንዳንድ የስጋ ነጋዴዎች በየጊዜው የኮንትሮባንድ ስጋ እያረዱ ለህዝብ ስለሚያቀርቡ መስሪያ ቤቱ በቅርብ በመከታተል ከ40 በላይ ጥፋተኞችን ለፍርድ አቅርቧል።

ለህዝብ ጤና ተስማሚ ያልሆነውን ከቄራ ውጪ የሚታረድ ስጋ ማቃጠል በህግ የተፈቀደ ነው በማለት የምእራብ ማዘጋጃ ቤት የጤና ጥበቃ መስሪያ ቤት ሹም አቶ ተረፈ ሀይሉ በሰጡት ዜና አስረዱ።

በጤናው ክፍል ሠራተኞች ተቆጣጣሪነት በየጊዜው ከሚያዙት ያለፈቃድ የታረዱ ከብቶች ስጋ ጋር የበሬ፣ የመሲና፣ የበግና የፍየል ቆዳዎች ተይዘው አብረው መቃጠላቸውም በዜና ተገልጧል።

**ጥር 1 ቀን 1963 ሰ.ም**

### በጥጥ ፍሬ ቅቤ ለመስራት ታቅዷል

በንፋስ ስልክ አካባቢ በመሰራት ላይ ያለው የጥጥ ፍሬ ዘይት ፋብሪካ ከዘይት ሌላ ማርጋሪን የተባለ ለዳቦ መብያና ለወጥ ማጣፈጫ የሚሆኑ የቅቤ አይነቶችን በተጨማሪ ለመስራት እቅድ እንዳለው የተባበሩት ዘይት ፋብሪካዎች ዳይሬክተር ሚስተር ኒኮላ ጆርጋአስ ገለጡ።

ፋብሪካው ስራውን የሚያካሂደው በአቶማቲክ መሳሪያ ሲሆን እስከአሁን ከግማሽ በላይ የሚሆነው ለፋብሪካው የሚያስፈልገው መሳሪያ መቅረቡንና ቀሪውም በቅርብ እንደሚመጣ ስራ አስኪያጅ ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

ፋብሪካው ከጥጥ ፍሬ የመብል ዘይት ይሰራል፤ ወደፊት የሀገር ውስጥ ፍላጎት ካረካ በኋላ ወደ አንዳንድ የጎረቤት ሀገሮችም ለመላክ ሀሳብ አለው። በየቀኑ እስከ 120 ቶን ጥጥ ፍሬ ለመጭመቅ ኃይል የሚኖረው ይህ ፋብሪካ ከሁለት ወር በኋላ ሥራ ይጀምራል። በዚህም ደረጃ ሥራውን ካካሄደ በቀን እስከ 13 ቶን ዘይት ሰርቶ ለማውጣት ይችላል ሲሉ ሚስተር ጆርጋአስ አስረዱ።

የዘይት ፋብሪካው አንዱ ዋና አላማ ይላሉ ሚስተር ጆርጋአስ ፤ እስከ አሁን በቂ አገልግሎት ላይ ሳይውል የቀረውን የጥጥ ፍሬ በሚጠቅም ተግባር ለማዋል ነው። ዘይቱ ከወጣ በኋላ የሚቀረውን አሰር ለከብት መኖ ወደ አውሮፓ በመላክ ለኢትዮጵያ አንድ የገበያ ምንጭ እንደሚሆን ይታመናል፤ የጥጥ ፍሬ ቁም ነገር ላይ መዋል የጥጥ ገበሬዎችን በይበልጥ ሊያበረታታቸው ይችላል።

በግማሽ ሚሊዮን ብር የሚሰራው ይህ ፋብሪካ ተፈጽሞ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የተባበሩት የዘይት ፋብሪካዎች ሠራተኞችን ቁጥር በአንድ መቶ ከፍ ያደርገዋል በማለት ሠራ አስኪያጁ ገልጠዋል።

**ጥር 8 ቀን 1963 ሰ.ም**

# ዓለም አቀፍ

## በድጋሚ የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ማክሮን ሕዝቡን አንድ ለማድረግ ቃል ገቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ኢማኑኤል ማክሮን ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲያገለግሉ በድጋሚ ተመረጡ።

ማክሮን እሁድ እለት በተደረገ አገር አቀፍ ምርጫ ተቀናቃኛቸውን ማሪን ሌ ፔንን በሰፊ ልዩነት አሸንፈዋል።

የቀኝ አክራሪዋ፣ ስደተኛ ጠል ናቸው የሚባሉት ማሪን ሌ ፔን ሊያሸንፉ የሚችሉበት ዕድል ስለነበረ የፈረንሳይ ምርጫ በተለይ በመላው አውሮጳ ከፍተኛ ትኩረት አግኝቶ ነበር።

ሌ ፔን ሙስሊም ሴቶች ሒጃብ በአደባባይ እንዳይለበሱ ሕግ የማውጣት ፍላጎት ነበራቸው።

ስደተኞችን የማባረር፣ ለአገሬው ሕዝብ በሁሉም ረገድ ቅድሚያ የመስጠት ፖሊሲም እንደሚከተሉ ቃል ገብተው ነበር።

በተጨማሪም ፈረንሳይ ከኔቶ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት እንዲሁም ከአውሮጳ ኅብረት የምትወጣበትን ሁኔታ እንደሚያፈላልጉ ለደጋፊዎቻቸው ቃል ገብተው ነበር።

ይህም በመሆኑ ነው የሳቸው አለመመረጥ በአውሮፓ ኅብረት አባል አገራት ዘንድ እፎይታን የፈጠረው።

ማክሮን በድጋሚ ፕሬዚዳንትነቱን ያሸነፉት ከድምጽ ሰጪው ሕዝብ 58.55 ከመቶ በማግኘት ነው።

ሌ ፔን ድምጽ ማግኘት የቻሉት ግን 41.45 የሚሆነውን ብቻ ነው።

ይሁንና ለአንድ ቀኝ አክራሪ ፓርቲ መሪ ይህን ያህል ድምጽ ማግኘት እጅግ ከፍተኛ የሚባል ሲሆን አገሪቱ ምን ያህል እንደተከፋፈለች የሚያመላክት ነው ይላሉ ተንታኞች።

ማክሮን ከድል በኋላ ባደረጉት ንግግር የተከፋፈለውን የፈረንሳይ ሕዝብ አንድ ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

ሌ ፔን ማግኘት የቻሉት 41.45 የሚሆነውን ድምጽ ነው።

ኢማኑኤል ማክሮን በተለይ ለመካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ዜጎች ደንታ የላቸውም፣ እሳቸው የሃብታም ፈረንሳውያን ፕሬዚዳንት ናቸው በሚል ሲወቀሱ ቆይተዋል።

ማክሮን የኑሮ ውድነትን መቆጣጠር አለመቻላቸውም ከፍተኛ ተቃውሞን አስነስቶባቸዋል።

የምርጫ ውጤቱ ይፋ ከሆነ በኋላ ሌ ፔን ሽንፈታቸውን የተቀበሉ ሲሆን ያገኙት ድምጽ በራሱ ግን ለፓርቲያቸው ትልቅ ድል እንደሆነ ተናግረዋል።

በአውሮጳ ከሚንቀሳቀሱ ቀኝ አክራሪ ብሔርተኞች ሌ ፔን ከፍ ያለ ስምና ዝና ያላቸው ቢሆንም እሳቸውም እንደ ወላጅ አባታቸው በተደጋጋሚ ተወዳድረው ድል ሳይሳካላቸው



ቀርቷል።

በተለይ በዚህኛው ዙር የሳቸው ፓርቲ ከሩሲያ ባንክ ብድር መውሰዱ፣ እሳቸውም ሩሲያ ክሪሚያን ጠቅልላ በወረራ ስትወስድ ድጋፍ ማሳየታቸውና ከቪላድሚር ፑቲን ጋር የተለየ ቅርበት ማሳየታቸው በምርጫ ክርክር ወቅት ከፍተኛ ነጥብ እንዲጥሉ ሳያደርጋቸው አልቀረም።

የምርጫው ውጤት ከተሰማ በኋላ የአውሮጳ አባል አገራት ከፍተኛ እፎይታ ተሰምቷቸዋል።

ምክንያቱም ሌ ፔን ምርጫውን አሸንፈው ቢሆን ሁነኛ የኔቶ አባልና የአውሮጳ ኅብረት አባል ፈረንሳይ ከኅብረቶቹ ልትወጣ የምትችልበት አጋጣሚ ይኖር ስለነበረ ነው።

ሌ ፔን የፑትንን ወረራ የመደገፍ አዝማሚያ ማሳየታቸው የአውሮጳ ኅብረት አባላትን አስቆጥቶ ነበር።

የማክሮንን ድል ተከትሎ የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን፣ የአውሮጳ ኅብረት ፕሬዚዳንት ቮን ደር ሌዮን እንዲሁም የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ደስታቸውን ገልጸዋል።

ዘለንስኪ ከምርጫው ቀደም ብሎም ቢሆን ፈረንሳውያን በፍጹም ለማሪን ሌ ፔን ድጋፍ እንዳያሳዩ፣ ይልቅ ለማክሮን ድምጽ እንዲሰጡ ተማጽነው ነበር።

ይህም የሆነው ተቀናቃኛቸው ማሪን ሌ ፔን ከፑቲን ጋር ያላቸው ቅርበት ስጋት ስለፈጠረባቸው ነበር።

የመራጮች ቁጥር በታሪክ ዝቅተኛ ከሚባሉት አንዱ ሆኖ የተመዘገበ የትናንቱ ድምጽ አሰጣጥ፣ 3 ሚሊዮን የሚሆኑ መራጮች ባዶ ወረቀት ምርጫ ኮሮጆ ውስጥ ዶለዋል ተብሏል።

ይህም የሚያመላክተው በርካታ መራጮች በሁለቱም ዕጩዎች ደስተኛ እንዳልነበረ ነው ይላሉ ተንታኞች።

ማክሮን በ20 ዓመታት የፈረንሳይ የቅርብ ታሪክ ለ2ኛ ጊዜ የተመረጡ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ናቸው።



## በሱዳን ዳርፉር ግዛት በተከሰተ ግጭት 168 ሰዎች መገደላቸው ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ግጭቱ የተከሰተው "አረብ ነን" እና "ጥቁር ነን" በሚሉ ሁለት ጎሳዎች መካከል ነው፡፡

በሱዳኗ ዳርፉር ግዛት በተከሰተ ግጭት ከ167 በላይ ሱዳናውያን ሲገደሉ 98 ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸው ተገልጿል።

በምዕራብ ዳርፉር ካሪናክ በትሰኘች ከተማ በተከሰተው ግጭት የሟቾች ቁጥር ወደ 200 ሊያሻቅብ ይችላል የተባለ ሲሆን፤ በርካቶች ደግሞ ከባድ አካላዊ ጉዳት እንደደረሰባቸው የስደተኞች እና ተፈናቃይ ኤጀንሲ ቢሮ ገልጿል።

ከሟቾቹ መካከልም ስድስቱ መምህራን ናቸው የተባለ ሲሆን፤ የግጭቱ መነሻ ባሳለፍነው አርብ "አረብ ነን" እና "ጥቁር ነን" በሚሉ ሁለት ጎሳዎች መካከል ተከስቶ የነበረው ግጭት በትናንትናው ዕለት ድጋሚ በማገርሸቱ ነው።

ይህ ጎሳን መሠረት ያደረገ ግጭት ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመስፋፋት ላይ ነው የተባለ ሲሆን፤ አልጀኒና ወደ ተሰኘው ሌላኛው የዳርፉር ከተማ ሰዎች በመጎዳት ላይ ናቸው ተብሏል።

በካሪናክ ከተማ የተከሰተውን ግጭት በመቃወምም በአጎራባች እና ሌሎች ከተሞች የሚኖሩ ሱዳናውያን መንገዶችን በመዝጋት ላይ መሆናቸው ተገልጿል።

በሱዳን ከሁለት ዓመት በፊት በዳርፉር በተከሰት የጎሳ ግጭት በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን በርካቶች ደግሞ ወደ ጎረቤት አገር ቻድ መሰደዳቸው ይታወሳል።

# ስፖርት

## ውድድርን በአሸናፊነት መደምደም ልምዷ እያረገች ያለችው አትሌት

ብርሃን ፈይሳ

እአአ በ2019 በሞሮኮ ራባት በተካሄደው የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ኢትዮጵያን ወክላ በተገኘችበት የግማሽ ማራቶን ውድድር ከስፖርት ቤተሰቡ ጋር ተዋወቀች፡፡ መንገዷን በስኬት የጀመረችው አትሌቷ አሸናፊነቷን የውድድሩ ክብረወሰን በሆነ ሰዓት (1:10:26) ደርባ ነበር ያስመዘገበችው፡፡

በተመሳሳይ በዚያው ዓመት በታላቁ የኢትዮጵያ ሩጫ ላይ የውድድሩን ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ ሁለተኛ ስኬቷን ለማጣጣም ችላለች፡፡ ከመነሻው ብቃቷን በማሳየት የስፖርት ቤተሰቡን በማሳመን በተለይ በጎዳና ላይ ሩጫዎች አገሯን በክብር እንደምታስጠራ ተስፋ ያሳየችው ይህቺ አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ትባላለች፡፡

ታታሪነት መገለጫዋ የሆነው አትሌቷ፣ በዚያው ዓመት በህንድ (ዴልሂ) እና በቻይና (ዚመን) ግማሽ ማራቶን ተሳትፎዎቿ የብር እና የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማስቆጠር ብቃቷን ማስመስከር ችላለች፡፡ በቀጣዩ ዓመትም በዴልሂ ግማሽ ማራቶን በድጋሚ ተሳትፎዋ አሸናፊ ስትሆን ቀድሞ ከገባችበት ሰዓት ሁለት ደቂቃ ማሻሻል ችላለች፡፡ በዓመቱ በግሏ ከተሳተፈችባቸው የግማሽ ማራቶን እና የ10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫዎች ባለፈ በፖላንድ በተካሄደው የዓለም ግማሽ ማራቶን ቻምፒዮና በድጋሚ አገሯን የመወከል ዕድል አግኝታ በግሏ የነሐስ ሜዳሊያ ስታጠልቅ፤ በቡድን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ለመሆን ችላለች፡፡

በመላው ዓለም በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በርከታ የአትሌቲክስ ውድድሮች ለመሰረዝና ለማራዘም ቢዳረጉም ያለምዘርፍ ግን ይህንን ጊዜ በስኬት ነበር ያሳለፈችው፡፡ ያለፈውን ዓመትም በተመሳሳይ በምርጥ አቋም ያሳለፈችው ሲሆን፤ በኢስታምቡል እና ቫሌንሺያ ግማሽ ማራቶኖች ተካፋይ ነበረች፡፡ በቫሌንሺያ የሮጠችበት 1:03:51 የሆነ ሰዓትም በርቀቱ የዓለም ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት የግሏ ነው፡፡

ይሁንና ዓመቱን ይበልጥ ስኬታማ ያደረገላት በአየርላንድ በተደረገው የአንተሪም ኮስት ግማሽ ማራቶን ያስመዘገበችው ሰዓት ነበር፡፡ ደስታና ኀዘን በእኩል በተንጸባረቁበት በዚህ ውድድር ያለምዘርፍ ርቀቱን የሸፈነችው 1ሰዓት ከ03 ደቂቃ ከ44ማይክሮ ሰከንድ በመሆኑ የዓለም ክብረወሰንን መስበር ችላለች፡፡ ነገር ግን በውድድሩ ላይ በድጋሚ በተደረገው ማጣራት የውድድሩ አዘጋጆች ርቀቱን በለኩበት ወቅት በተፈጸመ ስህተት ፈጣኑ ሰዓት እንደማይመዘገብ ይፋ ሊሆን ቻለ፡፡

ዜናው ከአትሌቷ ጥረትና ብቃት አንጻር ልብ ሰባሪ ቢሆንም ታታሪዋ ያለምዘርፍ ግን በቀላሉ እጅ የማትሰጥ መሆኗን አሳይታለች፤ ሁኔታው በድጋሚ በሌሎች ውድድሮች ተሳትፎዋ ህልሟን እውን ከማድረግ ሊያግዳት አልቻለም፡፡ በዚህ ዓመትም ሩጫዋን በታላቁ የኢትዮጵያ ሩጫ አሸናፊነት ነበር የጀመረችው፡፡ ከሁለት ወራት በፊትም በስፔን በተካሄደ የ10 ኪሎ ሜትር ሩጫ 24 ደቂቃ ከ29 ሰከንድ ከ14 ማይክሮ ሰከንዶች በመሮጥ የዓለም ክብረወሰኑን ከእጇ በማስገባት በድጋሚ ድሏን ለማጣጣም በቅታለች፡፡

በርካታ የዓለም ምርጥ አትሌቶችን ባቀፈው ‹‹ኤንኤን ማናጅመንት›› ስልጠና ቡድን አባል የሆነችውና በአሰልጣኝ ተሰማ አብሽሮ የምትሰለጥነው ብርቱዋ አትሌቷ፣ ግማሽ ማራቶንን ከ10 ጊዜያት በላይ በመሮጥና አሸናፊም በመሆን ከፍተኛ ልምድ አላት፡፡




አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሯን በአሸናፊነት አጠናቃለች፤

ከትናንት በስቲያ ደግሞ በጀርመን የሃምቡርግ ከተማ ሌላኛው የስኬት መንገዷን ጀምራለች፡፡ የጀመረችውን ውድድር በአሸናፊነት መደምደም ልምዷ የሆነው አትሌቷ አስቀድሞ በስፖርት ቤተሰቡ ባገኘችው ግምት መሠረት አሸናፊ ሆናለች፡፡ የገባችበት 2:17:23 የሆነ ሰዓትም በግሏ የማራቶን ፈጣን በሚል ሲያዝላት፤ እአአ በ2016 በአገሯ ልጅ መሰለች መልካሙ ተይዞ የነበረውን 2:21:54 የሆነ ሰዓት በማሻሻል የስፍራውን ክብረወሰን ለመረከብ ችላለች፡፡

ውድድሩ የተካሄደበት የአየር ሁኔታ ፀሐያማ ቢሆንም በዕለቱ የነበረውን ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በመጠቀም ያለምዘርፍ ከመነሻው በፍጥነት ሮጣለች፡፡ በሁለተኛው የርቀቱ አጋማሽ ፍጥነቷን ብትቀንስም እርሷን ትከተላት ከነበረችው አትሌት ወደ ዘጠኝ ደቂቃ የሚጠጋ ልዩነት እንደነበረው አትሌትስ የተሰኘው ድረገጽ በዘገባው አስነብቧል፡፡

አትሌቷ ከድሏ በኋላ በሰጠችው አስተያየት ‹‹ሃምቡርግ የመጀመሪያውን የማራቶን ውድድር ያደረኩበት ቦታ ሲሆን፤ ውድድሩ ፈጣን ቢሆንም ምቹ ነበር፡፡ ከተመልካች ይሰጠኝ የነበረው ድጋፍ ደግሞ በተለይ ረድቶኛል›› ብላለች፡፡


## የብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ቁጥር :- 05/2014

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ሸዋ ዞን ገንዘብ መምሪያና የፑል አገልግሎት ለሚሰጣቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ለ2014 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ፡-

1. የተሸከርካሪ ዘይትና ቅባት
2. የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ መሠረት በጥቅል ድምር ወይም በነጠላ ዋጋ አወዳድሮ ግዥ ለመፈጸም ይፈልጋል ::
   ስለሆነም የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሣተፍ የሚችሉ መሆኑን ይጋብዛል፡፡

**በዚህም መሠረት፡-**

1. በዘርፉ የተሠማሩበት ህጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ያላቸው
3. የግዥው መጠን ከብር 200,000.00 / ሁለት መቶ ሺህ ብር / በላይ ከሆነ ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
4. ተጫራቾች በጨረታው ለመሣተፍ ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው ::
5. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከሰሜን ሸዋ ዞን ገንዘብ መምሪያ ቢሮ ቁጥር 12 ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሠዓት ብር 100.00 / አንድ መቶ ብር / በመከፈል መግዛት ይችላሉ ::
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚወዳደሩበትን እያንዳንዱ ሎት የጠቅላላ ዋጋ 1% የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ /CPO/ ወይም በጥሬ ገንዘብ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በሰሜን ሸዋ ዞን ገንዘብ መምሪያ ሥም ማስያዝና ኮፒውን አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሃሣባቸውን በአንድ ወይም አንድ ወጥ በሆኑ ሁለት ቅጂዎች ማለትም ዋናና ቅጅ በማለት በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ በሰሜን ሸዋ ዞን ገንዘብ መምሪያ በግዥና ንብ/አስ/ቡድን ቢሮ ቁጥር 22 እስከ 16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
8. ጨረታው በ16ኛው ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡00 ሠዓት ታሽጎ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ይከፈታል :: ሆኖም የጨረታ መክፈቻው ዕለት የሥራ ቀን ላይ ካልዋለ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከላይ በተጠቀሰው በተመሣሣይ ሠዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
9. ማንኛውም ተጫራች የሚያቀርበው የመወዳደሪያ ሃሣብ በሌላኛው ተጫራች ዋጋ ላይ ተንተርሶ ማቅረብ የለበትም ::
10. የጨረታ ግምገማው እንደአስፈላጊነቱ በሎት በጥቅል ደምር የሚካሄድ በመሆኑ ተጫራቾች የሁሉንም ዕቃዎች የመጫረቻ ዋጋ በስፔስፊኬሽን / በናሙናው መሠረት ዋጋ ሞልተው መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡
11. በጨረታው ለመሣተፍ ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ከተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን በተጨማሪም በአካል ቢሮ ቁጥር 22 ወይም በስልክ ቁጥር 011-681-32-41 በመደወል መጠየቅ ይችላል::
12. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በመሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**የሰሜን ሸዋ ዞን ገንዘብ መምሪያ**
**ደ/ብርሃን**



## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

ኮርፖሬሽናችን ከዚህ በታች ለተጠቀሱት እቃዎች/አገልግሎት የመንግስትን ግዥ መስፈርቶች የሚያሟሉ እና በዘርፉ ከተሰማሩ ህጋዊ ድርጅቶች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ለምርት ጥራትና ቁጥጥር ለሚውል የተለያዩ ኬሚካል ግዥ 1ኛ ለምርት ጥራትና ቁጥጥር ለሚውል የተለያዩ ኬሚካል ግዥ የጨረታ ቁጥር፡- ኢንሥኮ-ማዕከል ግዥ ብግጨ15/2014

**ስለሆነም በጨረታ ሳይ መወዳደር የሚፈልጉ ድርጅቶች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው::**

1. ተጫራቾች በዘርፉ ለ2014 በጀት ዓመት የታደሰ የንግድ ፈቃድ ወይም ጨረታው እስከ ሚከፈትበት ቀን ድረስ ሊያገለግል የሚችል የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የአቅራቢነት ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ በጨረታ ለመሳተፍ የሚያስችል ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ወቅታዊ ክሊራንስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የግብር ከፋይ ምዝገባ ስርተፍኬት እና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን እነዚህ ሰነዶች በቴክኒካል ፕሮፖዛል ፖስታ ውስጥ ታሽገው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጫራቾች የፋይናንሻል ሰነዳቸውን ለብቻ በፖስታ በማሸግና የፋይናንሻል ሰነድ መሆኑን በመግለጽ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ከላይ የተገለጹትን ሰነዶች ከጨረታ ሰነድ ማቅረቢያው ቀነ ገደብ በፊት ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል ከሚያዚያ 21/2014 ዓ.ም ጀምሮ ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2፡00-6፡00 ሰዓት እንዲሁም ከሰአት ከ7፡00-10፡30 ሰዓት እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡00-6፡00 ሰዓት ድረስ ብሎክ 1 ቢሮ ቁጥር 206 ድረስ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡ (አድራሻው ከስር ተገልጿል፡፡)
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን እስከ ጨረታው መዝጊያ ዕለት እስከ ግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ድረስ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች ከላይ ለተጠቀሱት ጨረታ፡- ኬሚካል ግዥ ብር 50,000.00 (አምሳ ሺህ ብር) በሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ስም አሰርተው ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ አለባቸው፡፡ ኢንሹራንስ ቦንድና ቼክ ተቀባይነት የላቸውም፡፡
6. ተጫራቾች ለሚያቀርቧቸው ኬሚካል የቴክኒክ ሰነድ እና የፋይናንሻል ሰነድ ለየብቻ በፖስታ በማሸግና ኮፒ እና ኦሪጅናል የፋይናንሻል እንዲሁም የቴክኒካል ሰነድ ኮፒዎችን ለየብቻ በፖስታ በማሸግ በአንድ ላይ በትልቅ ፖስታ ሁሉንም ፖስታዎች በማድረግ ግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ተዘግቶ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በኮርፖሬሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡ አድራሻ ከታች ተገልጿል፡፡
7. ከዋና የመወዳደሪያ ሀሳብ (ኦሪጅናል) በተጨማሪ የሚፈለጉ ኮፒዎች ብዛት 1 (አንድ)
8. አሸናፊው ድርጅት የውል ማስከበሪያ መጠን 10 ፐርሰንት /አስር ፐርሰንት በካሽ፣ ሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ስም አሰርተው ውሉን የሚፈጽሙ ይሆናል፡፡
9. ኮርፖሬሽኑ ጨረታውን በከፊልም ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ለማንኛውም ማብራሪያ በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ በመደወል መጠየቅ ይቻላል፡፡ የግዥና ንብረት አስተዳደር ፋሲሊቲ ማኔጅመንት ቡድን አስተባባሪ
   ደብረዘይት መንገድ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ ፊት ለፊት ስልክ ቁጥር 011 416 73 45/011 466 9336

**የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**